# አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች  ትንተና  (በዳውሮ ዞን ሦስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)

በ

ኅርፍነሽ ታደሰ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

ድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

ሰኔ ፤ 2011 ዓ.ም

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሂውማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል

## ድሕረ ምረቃ መርሐ ግብር

# አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ትንተና (በዳውሮ ዞን ሦስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ተተኳሪነት)


**በ**

**ጎርፍነሽ ታደሰ**

**በአማካሪ**

**ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)**


**ሰኔ ፣ 2011 ዓ.ም**

**የፈታኞች ማረጋገጫ፤**

| የአማካሪ ስም | ፊርማ |
| --- | --- |
| -------------------------------- | --------------------------- |
| ---------------------------------- | ----------------------------- |

| **የፈታኝ ስም** | **ፊርማ** |
| --- | --- |
| **------------------------------** | **--------------------------** |
| **-------------------------------** | **---------------------------** |

## ምስጋና

ከሁሉ አስቀድሜ የማመሰግነው ይህን ጥናት ከፍጻሜ እንዳደርስ የረዳኝን እግዚአብሄርን ነው ፡፡

በመቀጠል ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጽሁፌን በማረም አስተያየትና ምክር በመስጠት ከፍተኛ እገዛና ድጋፍ ላደረጉልኝ ውድ አማካሪየ ለማ ንጋቱ (ዶ/ር) ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

እንዲሁም ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ሳከናውን ከጎኔ ሆነው በሞራል፣ በገንዘብና በማቴሪያል እየደገፈ ለዚህ ስራ መሳካት ትልቁን ሚና ለተጫወተ ውድ ባለቤተ ተሾመ ባቲሳን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡

በመቀጠልም የራሳቸውን አስተያየት በመስጠትና በተለያዩ ማቴሪያል ለደገፈኝ የታርጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ርዕሰ መምህር ሳላመሰግን አላልፍም ፡፡

## አህፅሮተ ጥናት / Abstract/

የጥናቱ ዋና ዓላማ አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መተንተን ነው፡፡የጥናቱ ተሳታፊዎች በደቡብ ብሔርብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በዳውሮ ዞን ሦስት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ2011 ዓ.ም በ9ኛ የክፍል ደረጃ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙት ከዘጠኝ ክፍል 600 ተማሪዎች መካከል በእድል ሰጪ ናሙና ዘዴ የተመረጡ 91 ወንድና 80 ሴት በድምሩ 171 ተማሪዎችና 4 አማርኛ መምህራን ናቸው፡፡ ጥናቱ መጠናዊ የምርምር ስልትን መሰረት ያደረገ ሲሆን የተከናወነው ገላጭ የአጠናን ስልት ተከትሎ ነው፡፡ መረጃው በፅሁፍ መጠይቅ፣ በክፍል ምልከታና በቃለመጠይቅ ተሰብስቧል፡፡ በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰቡት መረጃዎች በኤስፒ ኤስ ኤስ (spss) ስታስትክስ ነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት(One sample t-test) ቀመር ተሰልቶ ተተንትነዋል፡፡ በውጤት ትንተናው መሰረት የተማሪ ክፍል ተሳትፎ የሚወስኑ ተግዳሮቶች በክፍል ምልከታና ቃለ መጠይቅ የተገኘውን መረጃ ገላጭ የትንተና ዘዴ በመጠቀም ውጤቱ በመቶኛ ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ በዚህም መሰረት በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚወስኑ ተግዳሮቶች መኖራቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ በሌላ በኩል በክፍት የፅሁፍ መጠይቅ፣ በተማሪዎችና መምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ውጤት በተማሪዎች ቋንቋ ክሂሎት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር መሆኑንም የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡በጥናቱ ውጤት መሰረትም የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ለመቀነስ የሚያስችሉ የተለያዩ የአቀራረብ መንገዶችን በመከተል ትምህርቱን እንዴት ማቅረብ እንደሚገባ ለመምህራን ስልጠና ቢሰጥ፤ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚወስኑ ተፅዕኖዎችን በመቀነስ ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎት የሚያሳድጉበትን ምቹ ሁኔታ መምህራን ቢፈጥሩ መልካም ነው በማለት አጥኝዋ አስተያየተን እገልፃለሁ፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና .......................................................................................... I

አህፅኖተ ጥናት .......................................................................................... II

ማውጫ .......................................................................................... III

**ምዕራፍ አንድ**

1. የጥናቱ ዳራ .......................................................................................... 1

1.1የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት .......................................................................................... 4

1.2ጥናቱ የሚመልሳቸው መሠረታዊ ጥያቄዎች .......................................................................................... 7

1.3የጥናቱ አላማ.......................................................................................... 7

1.4የጥናቱ ጠቀሜታ .......................................................................................... 7

1.5የጥናቱ ወሰን .......................................................................................... 8

1.6የጥናቱ ውስንነት.......................................................................................... 8

1.7የጥናቱ ቁልፍ ቃላት ብያኔዎች.......................................................................................... 9

## ምዕራፍ ሁለት

## 2 ክለሳ ድርሳናትና የተዛማጅ ጽሁፎች ቅኝት ................................10

2.1 የክፍል ተሳትፎ ምንነት .......................................................................................... 10

2.1.1 የክፍል ተሳትፎ ጠቀሜታ.......................................................................................... 11

2.2 የተማሪ ክፍል ውስጥ ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶች .......................................................................................... 13

2.2.1 የተማሪ የራሱ ተግዳሮት.......................................................................................... 13

2.2.1.1 ተነሳሽነት .......................................................................................... 13

2.2.1.2 አመለካከት ........ 15

2.2.1.3 ስብዕና ........ 16

2.2.1.4 ጭንቀት ........ 19

2.2.1.5 ዖታ ........ 20

2.2.1.6 የተማሪዎች ቋንቋ ደረጃ ........ 21

2.2.2 የመምህሩ ተግዳሮት ........ 22

2.2.2.1 የማስተማሪያ ዘዴ ........ 22

2.2.2.2 የመምህሩ ባህሪ ........ 23

2.3.3 የመማር እና የማስተማር ሁኔታዎች ........ 24

2.3.3.1 የክፍል ውስጥ ተጨባጭ ሁኔታ ........ 25

2.3.3.2 የክፍል ውስጥ አየር ሁኔታ ........ 25

2.3.3.3 የተዛማጅ ጥናት ቅኝት ........ 26

## ምዕራፍ ሦስት

3. የጥናቱ ዘዴና አካሄድ ........ 28
3.1 የጥናቱ ንድፍ ........ 28
3.2 የጥናቱ አካላይ ........ 28
3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ ........ 28

3.3.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ ........ 28

3.3.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 29

3.3.3 የመምህራን እና ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 29

3.4 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ........ 29

3.4.1 የፅሁፍ መጠይቅ ........ 29

3.4.2 ምልከታ ........ 30

3.4.3 ቃለ መጠይቅ ........ 31

3.5 የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን ........ 31

3.5.1 የመረጃ አደረጃጀት ........................................................................ 31

3.5.2 የመረጃ አተናተን ........................................................................ 32

ምዕራፍ አራት IV

4 የጥናት ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........................................................ 33

4.1 የውጤት ትንተና ........................................................................ 33

4.1.1 ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ ........................................................ 33

4.1.2 የክፍል ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶች በክፍል ምልከታ

የተገኘ መረጃ ትንተና በነጠላ ናሙና ቲተስት .......................................... 34

4.1.3 በቃለ መጠይቅ ከተማዎችና እና ከመምህራን የተገኘ

መረጃ ትንተና ........................................................................ 43

4.1.3.1 ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ ትንተና .................................................. 43

4.1.3.2 ከመምህራን የተገኘ መረጃ ትንተና .................................................. 45

4.2 የውጤት ማብራሪያ ........................................................................ 47

4.2.1 በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ

ተግዳሮቶችን መፈተሽ ........................................................................ 48

4.2.2 በተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚወስኑ ተግዳሮቶች በቋንቋ

ትምህርት የሚያሳድረውን አንድምታ መመርመር ........................................ 57

ምዕራፍ አምስት

5 ማጠቃለያ የመፍትሄ ሀሳብ ........................................................................ 58

5.1 ማጠቃለያ ........................................................................ 58

5.2 የመፍትሄ ሀሳብ ........................................................................ 59

ዋቢ መጽሃፍች ........................................................................

አባሪዎች

አባሪ (ሀ) ለተማሪ የቀረበ የጽሁፍ መጠይቅ

አባሪ(ለ) ለተማሪ አንፃር ለክፍል ምልከታ የተዘጋጀ

አባሪ(ሐ) ከመምህራን አንፃር ለተማሪ ክፍል ተሳትፎ ምልከታ የተዘጋጀ

አባሪ(መ) ለተማሪ የተዘጋጀ ቃለ መጠይቅ

አባሪ(ሠ) ለመምህራን የተዘጋጀ ቃለ መጠይ

V

ማውጫ

4.1 በአማርኛ ትምህርት ጠተማሪዎች ዘኍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮት በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ማጠቃለያ ........ 34

4.2 ከተማሪዎች አንጻር የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮት ለመፈተሽ የተካሄደ የክፍል ውስጥ ምልከታ........ 38

4.3 ከመምህራን አንጻር የተማሪ ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመፈተሽ የተደረገ የክፍል ምልከታ ........ 41

4.4 የመማር ማስተማር ሁኔዎች በተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ ያለውን ተግዳሮት ........ 42

# ምዕራፍ አንድ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ በሁሉም ቦታ ሰዎች ለሥራም ይሁን ለማህበራዊ ኑሮ የሚያስፈልግ ቁልፍ መሣሪያ ነው፡፡ ከድሮ ዘመን ጀምሮ የሰው ልጆች ዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸውንና ተግዳሮቶቻቸ ውን ለሌሎች የሚያስረዱበት፣ በመንግስትም ሥራ ሆነ በሐይማኖት ተቋማት የሰዉ ልጆች ሀሳባቸውን የሚገልጹበት ተቀራርበው እንድኖሩ ካደረጋቸው ነገሮች ዋነኛው ቋንቋ ነው፡፡ በዓለም ደረጃ በበርካታ ቁጥር የሚቆጠሩ ቋንቋዎች አሉ፡፡ ከእነዚህ ቋንቋዎች ውስጥ ሰዎች አፋቸውን የፈቱበት ቋንቋና ሰዎች ተምረውና ተለማምደው የሚናገሩበት ሁለተኛ ቋንቋ ይገኛል፡፡

ሰዎች አፋቸውን የፈቱበት ቋንቋ የሚባለው ሰዎች ከተወለዱ በኋላ የሚናገሩበት የእናት አባታቸው መግባቢ ያ ቋንቋ ሲሆን ሁለተኛ ቋንቋ የሚባለው ደግሞ ሰዎች በራሳቸው አከባቢ ሆኖ ወደ ሌላ አከባቢ ሄደው ለሥራና ለማህበራዊ ኑሮ መግባቢያነት ተምረው ወይም ተለማምደው የሚና ገሩት ቋንቋ ነው፡፡

ሁለተኛ ቋንቋ በተለያዩ መንገዶች ሰዎች ሊማሩ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል በሚኖሩበት አከባቢ ከህብረተሰቡ ጋር ከቀን ወደ ቀን እየተለማመዱ የሚግባቡበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በትምህርት ቤት ገብተው የቋንቋውን ሙሉ ዕውቀት የሚያገኙበት ነው፡፡ በትምህርት ቤት ደረጃ ሁለተኛ ቋንቋ የሚሰጠው እንደ ልምድ የሚገኝ ለንግግር ፍጆታ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ከንግግር ጀምሮ ጽሁፍና ሌሎች በቋንቋው አስፈላጊ የሆኑ ባህርያትን የሚያውቁበት ነው፡፡

ቋንቋ ለሰው ልጅ የሚሰጠው ጠቀሜታ ብዙ ነው፡፡ የሰው ልጅ ሀሳቡን የሚገልፅበት፣ መልዕክት የሚያስተላልፍበት መሳሪያው ነው (Bailey & savage 1994)፡፡ ስለሆነም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አሳታፊ የማስተማር ዘዴ በመጠቀም ትምህርቱን ማቅረብና ተማሪዎችን እንዲሳተፉ ማድረግ የተማሪዎችን የትምህርት ተሳትፎ ከፍ የሚያደርግ ነው (sotto.1994 & Mohan.1993)፡፡

ከዚህ አንፃር በአገራችን በአሁኑ ጊዜ እየተተገበረ ባለው ስርዓተ ትምህርት ተማሪ አሳታፊ ማስተማር ዘዴ ትኩረት ተሰጥቶታል (በድሩ 1994)፡፡ እንደ ግንባታውያን ንድፈ ሀሳብ (constructivism theory)ተማሪዎች ቋንቋ መማር የሚችሉት ቀድሞ ባለው እውቀት ተመስርተው አዲሱን እውቀት ሲጨምሩ ነው (Stfen Krashen1982)፡፡ በመሆኑም እንደዚህ ንድፈ ሀሳብ አራማጆች እይታ ተማሪዎች አዲሱን መረጃ የሚያገኙት ቀድሞ ካላቸው እውቀት በመነሳት በክፍል እየሰሩ ሲማሩ ነው፡፡

በንድፈ ሀሳብ አራማጆቹ አመለካከት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቡድን ፣ በጥንድና በግል ተሳትፎ በማድረግ ሲማሩ አዲስ እውቀት ያገኛሉ፡፡ ስለዚህ መማር ስኬታማ የሚሆነው ተማሪዎች በተለያዩ መንገዶች እየተሳተፉ ሲማሩ ነው፡፡ እንደ Lee, (2005) አመለካከት በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የክፍል ተሳትፎ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጥያቄ በመጠየቅ፣ መልስ በመመለስ ፣ አስተያየት በመስጠት አንዱ ተማሪ ከሌላው ጋር በመወያየት የሚገለፅ ሲሆን በእነዚህ ተግባራት የማይሳተፉ ተማሪዎችን ፍዝ (Passive) ተብለው ይጠራሉ፡፡

የክፍል ተሳትፎ በመማር ማስተማር ሂደት የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ እውቀትና ክሂል ለማካበት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እርስ በርስ እና ከመምህራቸው ጋር የሚያከናውኑት ተግባር ሲሆን ጥያቄ በመጠየቅ ፣ በመወያየትና ግብረ መልስ በመስጠት የሚገለፅ ነው (Farrant,1990 Edward,2006)፡፡ Dbiss & Nestrmo (1985) የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመገኘት ሀሳባቸውን አሰባስበው ትምህርቱን በመከታተል፣ ከመፅሃፍ ጋር የቅርብ ወዳጅነት በማጠናከርና በመጠየቅ የእውቀት አድማሳቸውን እንዲያሰፉ የሚያግዝ ነው፡፡

Tatar,s.(2005) እና Green.(2008) እንዳብራሩት የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሀሳባቸውን በመግለፅ፣ ግልፅ ያልሆነውን ነገር በመጠየቅ ፣ አስተያየት በማቅርብ፣ የሌሎችን ሀሳብ በማድነቅ ወይም በመቃውም፣ የግል መረጃ በማቅረብ እርስ በርስ የሚማማሩበት፣ እውቀትና ክሂል የሚያዳብሩበት ነው፡፡ የክፍል ተሳትፎ ተማሪዎች ከጓደኞቻቸው እና ከመምህራቸው ጋር ያለፍረሃት፣ ነፃ ሆነው ጥያቄ በመጠየቅና በመመለስ ወይም ለትዕዛዞች መልስ በመስጠት የሚገለፅ ነው፡፡

እንደ Geeren አገላለፅ ተሳትፎ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የራሳቸውን ሀሳብ በነፃነት በመግለፅ ትምህርቱን ንቁ በሆነ መንገድ ለመማር የሚያስችል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡እንደ ምሁራኑ አገላለፅ የተማሪ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጥያቄ በመጠየቅ፣ በመመለስ፣ ሀሳብ በመስጠትና በመወያየት እርስ በርስ እና ከመምህራቸው ጋር ንቁ ተሳትፎ በማድርግ የሚፈፅሙበት ክሂልና እውቀት የሚያካብቱበት ነው፡፡ በመሆኑም ለቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

Warren, (1997) እንደጠቀሱት በመማር ማስተማር ሂደት የክፍል ተሳትፎ ማድረግ ተማሪዎች አዲስ ክህሎትን ለመማር ወሳኝ የሆኑ አጋጣሚዎችን ይፈጥራል፤ ለመማር ጠቃሚ የሆነ ጥልቅና ትርጉም ያለው ተዛምዶ በአዕምሮ ውስጥ ለመፍጠር ይረዳል፡፡

Peprena & pazake (2008) ተማሪዎች በቀጣይ ምን መማር እንዳለባቸው እንዲያስቡና እንዲገልፁ ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ ትምህርቱ በተማሪ ተሳትፎ የታጀበ ቢሆን የመማር ማስተማር ዓላማን ለማሳካት ያስችላል፡፡ በተመሳሳይ Hill.(2007) የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ የትምህርቱን ይዘት በበለጠ እንዲገነዘቡና ትምህርቱን ከራሳቸው ጋር እንዲያዋሂዱ ያግዛል፡፡

ለመማር ማስተማር ውጤታማነት ሂደት የሚያስፈልጉ ነገሮች መሟላትና አለመሟላት በተማሪ ሥነ ባህሪ ለውጥና ውጤት አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደር ይችላሉ፡፡ ለአብነት የሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትን በሚመለከት የሥርዓተ ትምህርቱ ይዘትና ዓላማ ከተማሪ ማስተዋል ደረጃ ጋር ተመጣጣኝ መሆን አለመሆን እንድሁም የመርሀ ትምህርትና የመጽሃፍ ዝግጅት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ከሥርዓተ ትምህሪቱ ጋር ግንኙነት ስላለው ተመሣሣይ ተጽዕኖ ማሳደር ይችላሉ፡፡

ከዚህ ውጭ የመምህራን የትምህርት ዕቅድና አቀራረብ ፣ የተማሪና የመምህሩ ግንኙነት እንድሁም የትምህርት ቤቱ ውስጣዊና ውጫዊ አከባቢ መመቻቸትና አለመመቻቸት በተማሪው ትምህርት ውጤትና ባህሪ ለውጥ ላይ የበኩላቸውን ሚና ይጫወታሉ:: Peprena & pazake (2008)፡፡

የትምህርት ቤቱን ውስጣዊ ጉዳዮችን ስንመለከት የክፍሉ ንጽህና ፣የመቀመጫና ጠረጴዛዎች አቅርቦት ፣ የተማሪ መጽሃፍ ጥምርታ ፣ የተማሪ ክፍል ጥምርታ ፣ የመምህር ተማሪ ጥምርታ ፣ የንባብ ክፍል ወይም ቤተ መጽሐፍት ዝግጅትና የአገልግሎት አሰጣጥ ፣ የመገኘት ፣ በተማሪ ውጤት ላይ አስተዋጽኦ ያበረክታሉ፡፡ ውጫዊ የትምህርት ቤት እይታን በሚመለከት ተማሪዎች በትምህርት ጊዜም ይሁን በትርፍ ሰዓት የሚጫወቱበት የስፖርት ሜዳና ፣ ማዘውተሪያ ሥፍራዎች፣ የንጹህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት፣ የተማሪዎችና የመምህራን፣ መፀዳጃ ቤት በጾታ ተለይቶ መኖር የኤሌክትሪክ ሀይል አቅርቦት ፣ የትምህርት መርጃ መሳሪያዎች አደረጃጀት በዋናነት ለትምህርቱ ሥራ አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው Hill.(2007)፡፡

በመማር ማስተማር ሂደትም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ የሚያግዱ ነገሮች የመማሪያ ክፍል ገፅታ ፣ የተማሪ ቁጥር መብዛት፣ ወንበር፣ ጠረጴዛ፣ የክፍል ውስጥ ብርሃንና ሠሌዳ ናቸው (Harmer፣ 2001፤ Le,Thi, mai፣ 2011)፡፡ በመሆኑም ብዙ ተማሪዎች ያለበት ክፍል ለመማር ማስተማር ሂደት ምቹ ካለመሆኑ የተነሳ የመማሪያ ግብዓት በበቂ ሁኔታ የማይገኝና በክፍል ውስጥም የተማሪ መምህር ግንኙነት የላላ ስለሚሆን ለክፍል ውስጥ ተሳትፎ አመቺ አይሆንም፡፡

በአጠቃላይ በዳውሮ ዞን ውስጥ በሚገኑ ትምህርት ቤቶች አማርኛ ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ከሦስተኛ ክፍል ጀምሮ እስከ አስረኛ ክፍል ድረስ የሚማሩት ቋንቋ ነው፡፡ በተለይም የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ወሰኑ በአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ሆኖ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ይመለከታል፡፡ በመሆኑም ተተኳሪ በሆኑት በዳውሮ ዞን አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ምን እንደሆኑ በጥናቱ ተተንትኗል፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

የቋንቋ ትምህርት በአብዛኛው የተማሪዎችን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው (Hill.2007) ፡፡ በክፍል ውስጥ የተማሪ ተሳትፎ መኖር ደግሞ ትምህርቱ ማራኪና ሳቢ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ተማሪዎች በንቃት ሲሳተፉ ደስታና እርካታ ይጎናፀፋሉ፡፡ Cohen,(1991)

እንደገለፁት በርካታ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሲያደርጉ እርካታ ስለሚሰማቸው የበለጠ ለመማር ይነሳሳሉ፡፡

በተመሳሳይ Tatar,S.(2005) እንደገለፁት ተማሪዎች በመማር ሂደት ተሳትፎ ሲያደርጉ የቋንቋ እውቀትና ክህሎት ያሳድጋሉ፤ ለቋንቋ ትምህርት የሚሆኑ ግብዓቶች ያፈልቃሉ፤ በክፍል እና ከክፍል ውጭ የተግባቦት ክህሎትን ያዳብራሉ፡፡ Stern, H. (1994) ተማሪዎች ተሳትፎ ሲያደርጉ ቋንቋ ለመማር ያላቸው ተነሳሽነትና ፍላጎት ይጨምራል፡፡

Green.D.(2008) በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት አዎንታዊ አመለካከት ይፈጥራል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ ትምህርት ያለ ተማሪ ክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ውጤታማ ይሆናል ለማለት የማያስደፍር መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

በሌላ በኩል በድሩ (1994) እንደገለፁት ያለ ተማሪ በቂ ተሳትፎ በመምህሩ አማካኝነት የሚተላለፍ ትምህርት በምንም ያህል ስፋትና ጥልቀት ተብራርቶ ሊቀርብ ቢችልም እንኳን ለተማሪ የሚሰጠው ጠቀሜታ ዝቅተኛ ነው፡፡ በመሆኑም የተማሪ ክፍል ተሳትፎ ሲኖር መማር ስኬታማ ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ማንኛውም የቋንቋ መምህራን ለተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ዕድል ቢሰጣቸው ጠቃሚ ነው፡፡ሆኖም የክፍል ተሳትፎ በብዙ ተግዳሮቶች ሊገደብ እንደሚችል ጸሐፍት ይገልፃሉ

(Petress,K.(2000)፤ Green. D.2008)፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የተማሪ ዕድሜ፣ ፆታ፣ ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት፣ ተነሳስቶ እና አመለካከት እንዲሁም የትምህርት አከባቢ ምቹ መሆን፣ የትምህርት ቤቱ አስተዳደርና አመራር፣ የተማሪ ቁጥር መጨመር የተማሪ መምህር መስተጋብር በክፍል ተሳትፎ ላይ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ፡፡

በሌላ በኩል Liu, (2005) በቻይና ውስጥ እንግሊዘኛን በሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ዝምታ በተመለከተ ባካሄዱት ጥናት በክፍል ውስጥ የተወሰኑ ተማሪዎች ተሳትፎ እንደሚያደርጉና አብዛኛው ተማሪ በክፍል ውስጥ በቡድንና በጥንድ ተሳትፎ ለማድረግ ፈቃደኛ አለመሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ በዋናነት የቋንቋ ችሎታ፣ ሰብዕና፣ ለመናገር ያላቸው ፍርሃት፣ ትምህርቱን ያለመረዳት፣ እሳሳታለሁ የማለት ስጋት፣ የመምህሩ ማስተማር ዘዴ እና የሚሰጣቸው ተግባራት ግልፅ ያለመሆን ችግር እንዳለ ይገልፃሉ፡፡

Liu,M, & Jackson,J.(2008) ተማሪዎች በንግግር ትምህርት ያላቸውን ፍርሃት አስመልክተው ባካሄዱት የቃኝ ጥናት ምልከታ እና ቃለ መጠይቅ አብዛኛው ተማሪዎች ለክፍል ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው ግንዛቤ ያነሰና ትምህርቱም በመምህራን ብቻ የሚቀርብ ገለፃ በመሆኑ አሳታፊነት እንደሚጎለው ይጠቁማሉ፡፡

በተመሳሳይ Li,H, & Liu,Y.(2011) እንደገለፁት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሃላፊነት መቀበልን ስለማይፈልጉ ዝምተኛ መሆንን ይመርጣሉ፡፡ ለዚህም የተማሪዎች በራስ መተማመን ማጣት፤ ዝግጅት ያለማድረግ፤ ስህተት ይፈጠራል ብሎ መፍራት፤ የቋንቋ እውቀት ያለመኖርና ሰብዕና በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ እንዳላቸው ያብራራሉ፡፡

ሌላው የተማሪ ተሳትፎ አስመልክቶ የተጠኑ ጥናቶች ስንመለከት ፋሲል (2002) የተማሪ ክፍል ተሳትፎ ላይ ክፍተት በመኖሩ ሊተኮር እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡ ሆኖም ዋና ትኩረታቸው በተማሪ ክፍል ተሳትፎና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ ላይ ነው፡፡

በተመሳሳይ ስፈራሽ (2002) በፅሁፍ መጠይቅና ምልከታ ባገኙት መረጃ መሰረት የክፍል ተሳትፎ ችግር እንዳለ እና መምህራን በቂ ዝግጅት እንደማያደርጉ ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም የክፍል ተሳትፎን በተመለከተ ያላለቀለትና ገና ጥናት የሚፈልግ ጉዳይ ነው፡፡

በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ የተካሄዱ ጥናቶች ለጉዳዩ ዘላቂ መፍትሄ ባለማግኘታቸው ጥናቱ በስፋትና በጥልቀት ያልተጠና በመሆኑ ተጨማሪ ጥናት የሚጋብዝ ነው፡፡ ስለዚህም አጥኝዋ ያገኘቻቸው ጥናቶች ተሳትፎን ከውጤት ተዛምዶና ከትምህርት አቀራረብ አንፃር ብቻ የመረመሩ በመሆኑና ተግዳሮቶችን ያልተመለከቱ በመሆኑ፣ አጥኝዋ የመረጠችው ርዕስ ከሌሎቹ ጥናቶች ይለየዋል፡፡

በተጨማሪም በክፍል ተሳትፎ ላይ እነዚህና ሌሎች መሰል ጥናቶች የተካሄዱ ቢሆንም ችግሩ እየተባባሰ እንጅ እየተቀረፈ እንዳልሄደ የተለያዩ ምሁራን ከሰነዘሩት ሀሳብና ከጥናት ውጤቶች መረጃ በማግኘተ የተማሪዎች የክፍል ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮት መተንተን ችግሩን ለመቅረፍ ያስችላል የሚል እምነት አሳድሯል፡፡ተማሪዎች በመማር ሂደት ተሳትፎ ሲያደርጉ የቋንቋ እውቀትና ክህሎት ያሳድጋሉ፣ ለቋንቋ ትምህርት የሚሆን ግብዓቶችን ያፈልቃሉ፣ ትምህርቱ ማራኪና ሳቢ እንዲሆን ያደርጋል፣ ተማሪዎችም ደስታና እርካታ ይጎናጸፋሉ፣ ከክፍል ውጭ የተግባቦት ክሂልን ያዳብራሉ፡፡ በመሆኑም አጥኝዋ በማስተማር

ስራ በቆየችባቸው ጊዜያት በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ጥያቄ ሲጠየቁ ፣መልስ ሲሰጡ ፣ እርስ በርስ እና ከመምህራቸው ጋር ሲወያዩ በተሰጣቸው ርዕስ ሲከራከሩ የክፍል ተሳትፎ ላይ ችግር መኖሩን  አስተውላለች፡፡ ከዚህ አንፃር ተማሪዎች ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመተንተን ወደ ጥናት ለመግባት ተነሳስታለች፡፡

ከዚህ አንፃር አጥኝዋ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ተማሪዎች ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ይኖር ይሆን ? በማለት ወደ ጥናት ለመግባት ተነሳስታለች፡፡

ስለዚህ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መተንተን የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት ነው፡፡

## 1.3 ጥናቱ የሚመልሳቸው መሰረታዊ ጥያቄዎች

1. በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ምንድ ናቸው?

2 .እነዚህ ተግዳሮቶች በቋንቋ ትምህርቱ ላይ የሚኖራቸው አንደምታ ምንድ ነው?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

- የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በዳውሮ ዞን ከሚገኙ አጠቃላይና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ትምህርት ጊዜ የክፍል ሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መመርመር ሲሆን  የሚከተሉት

  ዝርዝር አላማዎች አሉት፡፡
  - ✓ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መለየት፤
  - ✓ እነዚህ ተግዳሮቶች በተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ላይ የሚኖራቸውን አንድምታ መተንተን

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን በመተንተን መምህራን በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ተሳትፎን

የሚገድቡ ነገሮችን ለይተው እንዲተገብሩ ያግዛል፡፡ ስለሆነም ጥናቱ ለቋንቋ መምህራን ሆነ ለወረዳ፣ ለዞን፣ ለክልል ትምህርት ባለሙያዎች የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል፡፡

ሀ. ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን በክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን በመጠቆም በመማር ማስተማር ሂደት ትኩረት እንዲሰጡ መረጃ ይሰጣል፡፡

ለ. ወደ ፊት ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጥናት ለሚያጠኑ ለሌሎች አጥኝዎች መነሻ ሆኖ ያገልግላል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

በጥናቱ ተሳታፊ የሆኑት በደቡብ ብሔርብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት በዳውሮ ዞን ከሚገኙት 15 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሦስቱ ማለትም ታርጫ ፣ ቱሪ ና ማረሚያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በ2011 ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ያሉ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችና መምህራን ናቸው፡፡ ጥናቱ የሚያተኩረው በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ምን እንደሆኑ በመተንተን ቀደም ሲል በአነሳሽ ምክንያት ላይ ለተነሱ ጥያቄዎችን ይመልሳል፡፡ ከዚህ አንፃር የጥናቱ ትኩረት ከመምህሩ፣ ከተማሪና ከመማር ማስተማር ሁኔታዎች አንፃር ክፍል ወስጥ ተሳትፎን በሚገድቡ ተግዳሮቶች ላይ ብቻ ነው፡፡ይህ ጥናት የክፍል ውስጥ ተግዳሮት ሊሆኑ የሚችሉትን እንጂ ከዛ ወጭ ያሉትን አያካትትም፡፡ በተጨማሪም ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮትን መግለፅ እንጂ የምክንያትና ውጤት ግንኙነትን አይመለከትም፡፡

## *1.7. የጥናቱ ውስንነት*

ይህ ጥናት በደቡብ ብሔርብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት በዳውሮ ዞን ካሉት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በሦስት ትምህርት ቤት የሚዳሰስ በመሆኑ በዞኑ የሚገኙ ሌሎች የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን አለማካተቱ፤ በክፍል ውሰጥ ተሳትፎን ከሚገድቡ ተግዳሮቶች ውጭ ለሎችን ያለማየቱና በዘጠነኛ ክፍል ላይ ብቻ ማተኮሩ የጥናቱ ውሱንነት ሊታይበት ይችላል፡፡

## 1.7 ቁልፍ ቃላት ብያኔዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ አገልግሎት የሰጡ መሰረታዊ ሀረጋት ጽንሰ ሀሳብ እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

- **የክፍል ውስጥ ተሳትፎ** (Classroom Participation)

  ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ የሚያከናዉኗቸውን ተግባራት የሚመለከት ሲሆን በመጠየቅ፣ መልስ በመስጠት ፣በቡድን ውይይት ተሳትፎ ማድረግ ምሳሌዎችን መስጠት ወዘተ ለመሳተፍ የሚያደርጉትን ሙከራ የሚያካትት ይሆናል፡፡

- **ተግዳሮቶች** (challenges)

  ተማሪዎች የክፍል ተሳትፎ በሚያደርጉበት ጊዜ ተሳትፎን የሚገድቡ እንቅፋቶችን የሚመለከት ነው፡፡

- **መስተጋብር**

  ተማሪዎች ከመምህራኖቻቸው ወይም እርስ በርስ የሚያደርጉት የሀሳብ ልውውጥ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

## 2. ክለሳ ድርሳናትና የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

በዚህ ክፍል አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ ተማሪዎች አማርኛ ሲማሩ የክፍል ተሳትፎን የሚገድቡ የክፍል ተሳትፎ ምንነት፣ ጠቀሜታና የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች የያዘ ሲሆን ከተማሪ ከመምህርና ከመማር ማስተማር ሁኔታዎች አንፃር የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች በውስጡ ተካቷል፡፡

## 2.1 የክፍል ተሳትፎ ምንነት

የክፍል ተሳትፎ ማለት በመማር ማስተማር ሂደት የትምህርት ዓላማ ለማሳካት ተማሪዎች እርስ በርሳቸው ወይም ከመምህራቸው ጋር የሚያደርጉት መስተጋብር ሲሆን ተማሪዎች በተናጠልና በጥንድ እንዲሁም በቡድን ተግባራት ላይ የሚያሳዩትን እንቅስቃሴን የሚያካትት መሆኑን Farrant (1980) ፤Edward (2006) ይገልፃሉ፡፡

በተመሳሳይ Lee. (2005) & Ferteschenr. (2000) እንደገለፁት የክፍል ተሳትፎ የሚባለው ብዙውን ጊዜ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ጥያቄ ለመመለስ፣ ለመጠየቅ፣ አስተያየት ለመስጠትና በውይይት ለመሳተፍ የሚያደርጉት ንግግር ሲሆን በተጠቀሱት መንገዶች የማይሳተፉ ተማሪዎች ፍዝ (passive) ተማሪዎች ሲሰኙ የሚሳተፉት ደግሞ ንቁ (active) ተማሪዎች ይባላሉ፡፡

Rocca, (2009)፤ Petres (2000)ን ጠቅሰው እንደገለፁት ተሳትፎ ባለሁለት ፈርጅ ሲሆን አንድ ተናጋሪና አድማጭ ወይም ለንግግሩ ምላሽ የሚሰጥ አካል ያለበት ነው፡፡ ይህንን ሀሳብ በመደገፍ Rocca (2009) የክፍል ተሳትፎ በሁለትና ከዚያ በላይ ባሉ ግለሰቦችና ቡድኖች መካከል የሚደረግ ቃላዊ ምልልስ ወይም ንግግር መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም Warren (1997) እንደገለፁት የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ መገኘት ብቻ ሳይሆን ሀሳባቸውን አሰባስበው ትምህርቱን መከታተል ከመፅሐፍት ጋር የቅርብ ወዳጅነት ማጠናከር፣ መጠየቅና የዕውቀት አድማስን

ማስፋት ነው፡፡ በተመሳሳይ ስፍራሽ (2002) እንዳስረዱት የተማሪ ተሳትፎ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት በንቃት የሚያከናውኑትን ተግባር የሚመለከት ነው፡፡ ይኸውም ጥያቄ መጠየቅ፣ መልስ መስጠት፣ አስተያየት መስጠት፣ የቡድን ውይይት መምራት፣ ለሚታዘዙት ተግባር ቀና ስሜት መኖር፣ የቤትና የክፍል ስራዎችን መስራት የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በመሆኑም በመማር ማስተማር ሂደት መማር ስኬታማ እንዲሆን ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ ተሳትፎ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ያለምንም ጫና በፈቃደኝነት የሚያደርጉት የእርስ በርስ ምላሽ ነው (Burchfield & Sappington1999)፡፡

ይህንን ሀሳብ በመደገፍ Fassinger, (1995a) ተሳትፎ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በፈቃደኝነት ጥያቄ ለመጠየቅ፣ ምላሽ ለመስጠት፣ አስተያየት ለመስጠት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ በሙሉ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ በማጠናከር Fritschener. (2000) የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከቀላል የመማር ባህሪ እስከ ሙሉ ወይም አጠቃላይ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት የሚደርስ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

በተመሳሳይ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚደረግ የመምህርና የተማሪ፣ የመምህርና የቡድን ወይም አጠቃላይ ተማሪዎች፣ የተማሪ እና ተማሪ እርስበርስ ንግግር በተሳትፎ ውስጥ እንደሚካተት Smith. (1992) ይገልፃል፡፡

በተመራማሪዎች እይታ ተሳትፎ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቡድኖች ወይም ግለሰቦች መካከል የሚደረግ የእርስበርስ ግንኙነት ሲሆን የክፍል ተሳትፎ በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ጥያቄ በመጠየቅ፣ ለጥያቄ መልስ በመስጠት፣ አስተያየት በመስጠት፣ በመወያየት፣ በመተቸት እርስበርስና ከመምህራቸው ጋር የሚያከናውኑትን ተግባር  በሙሉ የሚያካትት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

### 2.1.1 የክፍል ተሳትፎ ጠቀሜታ

በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ማሳተፍ በርካታ ጠቀሜታ እንደሚሰጥ ፀሐፍት ይገልፃሉ (Cohen. 1991፤ Weaver. Qi, 2005)፡፡ እንደ ፀሐፊዎቹ ገለፃ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተማሪዎች በትምህርት ተግባራት ንቁ እንዲሆኑ የሚያደርግ፤ ለመማር ማስተማር ህይወት የሚሰጥ፤ ተማሪዎችን የበለጠ የሚያነሳሳ፤ የተሻለ እንዲማሩ የሚያደርግ እና ተማሪዎች የግል መረጃቸውን እንዲያቀርቡ የሚያበረታታ ነው፡፡

በተመሳሳይ ተማሪዎች የበለጠ የሚሳተፉ ከሆነ በትንሽ ትውስታ እንዲማሩ የሚያስችል፣ በከፍተኛ ደረጃ እንዲገናዘቡ የሚያደርግ፣ አንድን ነገር እንዲተነትኑ፣ እንዲያጠቃልሉ፣ ሀሳብን አያይዘው እንዲገልፁ የሚያግዝ እና የንግግር ክህሎታቸውን እንዲያሻሽሉ የሚረዳ መሆኑን Browen. (1994) ፣ Smith. (1992) ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በስፋት የተለማመዱበትንና በንቃት የተሳተፉበትን የትምህርት ይዘት በተሻለ ሁኔታ ሊገነዘቡት ይችላሉ (Bailey & Savage. 1994)፡፡ በተመሳሳይ Fassinger.(1995a) እንደጠቀሰው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በንቃት የሚሳተፉ ከሆነ ዕውቀታቸውን እንዲያዳብሩና በትምህርት ውጤታማ እንዲሆኑ ያግዛል፡

በመማር ማስተማር ሂደት የክፍል ተሳትፎ ማድረግ ተማሪዎች አዲስ ክህሎትን እንዲማሩ ወሳኝ የሆኑ አጋጣሚዎችን ይፈጥራል፣ ለመማር ጠቃሚ የሆኑ ጥልቅና ትርጉም ያለው ተዛምዶ በአዕምሮ ውስጥ ለመፍጠርም ይረዳል (Warren. 1997) ፡፡

Weaver & Qi (2005) እንደገለፁት የክፍል ተሳትፎ ተማሪዎች በቀጣይ ምን መማር እንዳለባቸው እንዲያስቡና እንዲገልፁ ዕድል የሚሰጥ በመሆኑ የመማር ማስተማር ዓላማን ለማሳካት ያስችላል፡፡ በተመሳሳይ Hill.(2007) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ቢያደርጉ የትምህርት ይዘትን የበለጠ እንዲገናዘቡና ትምህርቱን ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱ የሚያግዝ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ Petress.(2000) እንዳስረዳው የተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ተማሪዎች ትምህርቱን የበለጠ እንዲማሩና እንዲያስታውሱ ያስችላቸዋል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎች የተሻለ ሊማሩ የሚችሉት በመስራትና በመሳተፍ እንዲማሩ ሲደረግ ነው፡፡ እንዲሁም መማር ሳቢና ማራኪ የሚሆነው ተማሪዎች በትምህርት ሂደት ንቁ ተሳትፎ ሲኖራቸው ብቻ ነው፡፡

በመሆኑም መምህራን ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት በጥያቄና መልስ፣ አስተያየት በመስጠት በመወያየት እና በመተቸት እንዲሳተፉ ማድረግ ለተማሪዎች እና መምህራን ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ከላይ ከተጠቀሱት ፀሐፍት ገለፃ መረዳት ይቻላል፡፡

## 2.2 የተማሪ ክፍል ውስጥ ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶች

የተማሪ ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከተለያዩ ተግዳሮቶች አንፃር ሊወሰኑ እንደሚችሉ ጥናቶች ይጠቁማሉ (Steren 1994፤ Browen. 2000፤ Le; Thi; Mai 2011)፡፡ የተማሪ ክፍል ተሳትፎ ከተማሪ፣ ከመምህርና ከመማር ማስተማር ሁኔታዎች አንፃር በሚከሰተው ተፅዕኖ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ በሆነ መንገድ ሊወሰን እንደሚችል Le; Thi; Mai (2011) ይገልፃሉ፡፡

### 2.2.1 የተማሪ የራሱ ተግዳሮት

በመማር ማስተማር ሂደት ከተማሪ አንፃር የሚመጡ ተግዳሮቶች የክፍል ተሳትፎን ሊወስኑ ይችላሉ (Le.Thi.Mai 2011) ፡፡ ከተማሪ አንፃር ተግዳሮት የሚሆኑት የተማሪ አመለካከት፣ ተነሳስቶ፣ ሰብዕና፣ ጭንቀት፣ ዕታና የተማሪዎች ቋንቋ በክፍል ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተግዳሮት በመሆን ተሳትፎን ሊወስኑ እንደሚችሉ Browen (2000፤ 1994) ፤ Light bown, & Spada (2006) ያስረዳሉ፡፡

#### 2.2.1.1 ተነሳሽነት

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት የተማሪ ተነሳሽነት መኖር ወሳኝ ነው፡፡ ተነሳሽነት አንድ ሰው ለመማር በውስጡ እንዴት ተቀስቅሶ እንደሆነ የሚያመለክት ነገር ነው፡፡ ሆኖም ይህ ሁኔታ በአንዳች ምክንያት አነስተኛ የሆነ እንደሆነ የመማር ማስተማር ሂደት የተዳከመና ብቃት የጎደለው እንደሚሆን Farrant. (1980) ያስረዳል፡፡

ተነሳሽነት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሊወስን እንደሚችል Browen (1994)፤ Stern, (1994)፤ Light bown, & Spada (2006) ይገልፃሉ፡፡ ተነሳስቶ እንደማንኛውም የሰው ልጅ ባህርይ አብሮ የሚያድግ በሰው ልጅ ላይ የሚታይ ተፈጥሯዊ የሆነ አንድን ነገር ለመተግበር የሚያስችል ውስጣዊ ግፊት መሆኑን Browen (1994)፤ Harmer (2001)፤ Dornyei, (2005) ገልፀዋል፡፡ አዎንታዊ አመለካከትና ተነሳስቶ ስኬታማ ቋንቋ መማር ጋር እንደሚያያዝ Browen. (2000) የተጠቀሱት Gardner (1985) ይገልፃሉ፡፡ በሌላ በኩል አሉታዊ አመለካከት ለትምህርት ያላቸውን ተነሳስቶ ያሳንሳል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ የራሳቸው የሆነ አላማ አላቸው፡፡ ዋናዎቹ አላማዎች ከታላሚው ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር ማህበራዊ ውህደት ለመፍጠር ወይም ቋንቋ ጥቅማጥቅም ለማግኘት እንደሆነ Browen (1994) ፤Stern, (1994) ፤Gardner (1985) ይገልፃሉ፡፡

ትስስራዊ ተነሳሽነት ተማሪዎች ከቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ጋር ትስስር ለመፍጠር ወይም ቅርርብ ለመፍጠር በማሰብ ቋንቋውን ለመማር የሚነሳሱበት የተነሳሽነት አይነት ነው Gardner (1985)፡፡ ተማሪዎች ለቋንቋ ተናጋሪዎች ቋንቋና ባህል ማህበራዊ አኗኗር ወዘተ መልካም አመለካከት ካላቸው ቋንቋን ለመማር የሚኖራቸው ተነሳሽነት ጠንካራ እንደሚሆን አጥኚዎች ያስገነዝባሉ Gardner (1985)፡፡ ከግልጋሎታዊ ተነሳሽነት ይልቅ ትስስራዊ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ቋንቋን በተሻለ ሁኔታ ይማሩታል የሚል እምነት እንዳላቸው (Steren 1994) ይገልፃሉ፡፡

ግልጋሎታዊ ተነሳሽነት ተማሪዎች በቋንቋ አንዳች ግልጋሎት ለማግኘት ቋንቋን የሚማሩበት የተነሳሽነት አይነት ነው (Gardner. 1985) ፡፡ ተማሪዎች ቋንቋ የሚማሩበት ዓላማ የተለያየ ሊሆን ቢችልም ብዙን ጊዜ ለትምህርት መግቢያ ውጤት ማሟላት፣ የተሻለ ክፍያ ማግኘት፣ አለማቀፋዊ መረጃና እውቀት ማግኘት ዋናዋና የሚባሉ የግልጋሎታዊ ተነሳሽነት ዓላማዎች መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡

በተመሳሳይ Harmer, (2001) እንደጠቀሱት ተማሪዎች ለመድረስ ከሚፈልጉት ግብ አንፃር ተነሳስቶን ውስጣዊና ውጫዊ በማለት በሁለት ይከፈላሉ፡፡ ውሰጣዊ ተነሳሽነት ከግለሰቡ ራሱ የሚመጣ ሲሆን በቋንቋ ለመዝናናት እና ታላሚ ቋንቋ ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ሲሆን ውጫዊ ተነሳሽነት ደግሞ ፈተና ለማለፍ፤ ሽልማት ለማግኘት ሲሉ የሚማሩት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ተነሳሽነት ተማሪዎች ትምህርቱን ሲማሩ ከሚኖራቸው ግብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው፡፡ ግባቸው ዘለቄታ ያለው ከሆነ እዚያ ግብ ላይ ለመድረስ ሲሉ በትምህርታቸው ጠንካራ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ በአንፃሩ ግባቸው የውስንነት ባህርይ ካለው ተነሳሽነታቸው የደከመ ይሆናል፡፡ ይህም በትምህርትነት የሚሰጣቸውን ይዘት ፈተና ለማለፍ ብቻ የሚማሩ መሆናቸውን ይገልፃሉ (Farrant 1980) ፡፡

Schumann. (1975) እንደገለፀው ተነሳሽነት አንድን ተግባር ለማከናወን ከተማሪ ውስጣዊ ስሜት ፈንድቶ የሚወጣ ከመሆኑ የተነሳ ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ተነሳሽነት ከሌላቸው የሚማሩትን ትምህርት በነቃ ተሳታፊነት ሊከታተሉት አይችሉም፡፡ ተነሳሽነት ያላቸው ተማሪዎች ከመምህራቸው ጋር በቀላሉ ይግባባሉ፡፡ በክፍል ውስጥ ከተማሪዎች ሆነ ከመምህሩ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ለመመለስ ይጥራሉ፡፡ የመማሪያ መሳሪያዎችን በአግባቡ ይጠቀማሉ፡፡ በመምህራቸው ላይ እምነት ስለሚኖራቸው በመምህሩ ተዘጋጅተው የሚቀርቡ ትምህርቶችንና የማስተማሪያ ዘዴዎችን ይቀበላሉ፡፡ ተቃዋሚዎች አይሆኑም፤ ሳይሰላቹ የሚታዘዙትን ሁሉ ያከናውናሉ፡፡

ተነሳሽነት የሌላቸው ተማሪዎች ተነሳሽነት ካላቸው ተማሪዎች ተቃራኒ የሆነ ባህርይ ይታይባቸዋል፡፡ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚማሩት ትምህርትም ሆነ ለመምህራቸው ግድ የላቸውም፡፡ የሚታዘዙትን ለመስራት ከውስጥ የመነጨ ፍላጎት አይኖራቸውም፡፡ አዘውትሮ በትምህርት ገበታ ላይ አይገኙም በማለት Schumann. (1975) ገልፀዋል፡፡

ከዚህ በመነሳት በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች ካላቸው አላማ አንፃር የቋንቋ ትምህርት ሲማሩ ተነሳሽነት መኖር ወይም አለመኖር በመማር እና በተማሪ ክፍል ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ በማድረስ ተማሪዎች ቋንቋ በመማር ሊደርሱበት የሚያስቡትን ጉዳይ ከግብ እንዲያደርሱ ወይም እንዳያደርሱ ቁልፍ ሚና እንዳለው ከላይ ከተጠቀሱት ፀሐፍት ገለፃ መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.2.1.2 አመለካከት

በቋንቋ መማር ሂደት የተማሪዎች አመለካከት አስፈላጊ ነው፡፡ አመለካከት ለተለያዩ ሰዎች፣ ነገሮች ወይም ሁኔታዎች አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ምላሽ ለመሰጠት የሚያስችል ውስጣዊ አስተሳሰብ ነው፡፡ ይህ ውስጣዊ አስተሳሰብ ደግሞ በግለሰቦች ገለፃ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ግለሰቦች ለአንድ ነገር የሚሰጡትን ግምገማ ይመለከታል (Gardner & Lambrt 1972)፡፡ ማንኛውም የግምገማ ስሜት የሚፈጥር ነገር ደግሞ ለአንድ ጉዳይ ወይም ሁኔታ አመለካከት እንዲኖር ያደርጋል፡፡ ግምገማው ነገሮችን በመውደድ ወይም በመጥላት፣ በመቃወም ወይም በመደገፍ፣ በመስማማት ወይም ባለመስማማት፣ አሉታዊ ወይም አዎታዊ የሆኑ መልሶችን በመስጠት ይገለፃል (Schumann.1975)፡፡

በተጨማሪም በቋንቋ መማር ሂደት ተግዳሮት ከሚሆኑ በርካታ ምክንያቶች መካከል በሰዎች ላይ አብሯቸው የሚያድግ ስለ አንድ ነገር የሚኖራቸው አመለካከት አንዱ ነው (Steren 1992፣Brewn 1994)፡፡ በተለይም ባህላዊ፣ ማህበራዊና በቋንቋ ላይ የሚኖረው አመለካከት በቋንቋ መማር ሂደት ተማሪዎች ለትምህርቱ የሚኖራቸውን እይታ ያመላክታል (Schumann 1975)፡፡

ከዚህም ሌላ በአመለካከትና ቋንቋ ትምህርት መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ Gardner & Lambert (1972) ከዚያም Schumann (1975) ባካሄደው ጥናት ሁለት በጣም ጠቃሚ አመለካከት እንዳለ ያምናሉ፡፡ የመጀመሪያው ተማሪዎች ቋንቋን ለሚናገረው ማህበረሰብ እንዲሁም ቋንቋ ለሚወክለው ባህል የሚኖር አመለካከት ሲሆን ሁለተኛው ቋንቋን ለግል ጥቅማቸው ለማዋል ወይም ከግለሰቡ ፍላጎት ጋር በተያያዘ ያላቸው አመለካከት ነው፡፡ የመጀመሪያው አይነት አመለካከት ሁል ጊዜ ከውጤት ጋር የተያያዘ ሲሆን ሁለተኛው አይነት አመለካከት ከብዙ ተላውጦዎች ጋር ካለው ዝምድና አንፃር የሚታይ ነው (Schumann 1975)፡፡

በተጨማሪም Schumann (1975) ተማሪዎች በተለይ ለቋንቋ ያላቸው እይታ ጥሩ ከሆነ አመለካከታቸው አዎንታዊ ይሆናል፡፡ በተቃራኒ ያላቸው እይታ መጥፎ ከሆነ አሉታዊ ይሆናል፡፡በሁለተኛ ቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳታፊ ሲሆኑ አሉታዊ አመለካከት ያላቸው ተማሪዎች ለትምህርቱም ሆነ ለክፍል ተሳትፎ ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ ነው ፡፡

## 2.2.1.3 ስብዕና

ሰብዕና የሰው ልጅ አንዱ ከሌላው የሚለይበት አንዱና ዋንኛው ባህሪይ እንደሆነ Dornyei (2005) ይገልፃሉ፡፡ እንደ ኮሊንስ ኮባልድ መዝገበ ቃላት አገላለፅ ሰብዕና ተፈጥሯዊ እና የሰው ልጅ ሙሉ ባህሪይ ነው፡፡ ሰብዕና አንድን ግለሰብ ከሌላው የሚለየው ብቸኛ መለያ ነው፡፡ Browen (2000) እንደገለፁት ሰብዕና የሰው ባህርይ፣ ስሜት፣ ግንዛቤና ፀባይ የሚወክል ነው፡፡ በተጨማሪም የተማሪዎች የሰብዕና ልዩነት በቋንቋ ትምህርት በተማሪ ክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት እንዳለው ያስረዳሉ፡፡

በብዙ ተመራማሪዎች ዕይታ ሰብዕና ለቋንቋ ትምህርት ስኬትና ውድቀት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያለውና ዋንኛ ተግዳሮት አድራሽ መሆኑን Schumann (1975) ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ሰብዕና በተማሪ ክፍል ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተግዳሮት አለው፡፡ የተማሪ ሰብዕና የሚታየው ከተማሪው ባህርይ አንፃር ሲሆን በአብዛኛው በተማሪ ክፍል ውሰጥ ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት የሚሆኑ የስብዕና ባህርያት ተሳታፊነትና ጭምትነት፣ ኃላፊነት መቀበል፣ ለራስ ከበሬታ መስጠት የሚጠቀሱ እንደሆኑ Browen, (2000) Dornyei. (2005)፤ Lightbown, & Spada (2006) ይገልፃሉ፡፡

ተሳታፊነት የስብዕና ባህሪ ያላቸው ተማሪዎች ከብዙዎች ጋር ግንኙነት መፍጠር የሚችሉ፣ ብዙ ጓደኛ ያላቸው፣ ስሜት ፈጣሪዎች፣ ኃላፊነት ተቀባዮች፣ ቀልደኞች እና ማህበራዊነት ያላቸው ሲሆኑ በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፊዎች ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ጭምትነት የሰብዕና ባህርይ ያላቸው ተማሪዎች ከሌሎች ጋር ከመነጋገር ይልቅ ዝምተኝነትን የሚመርጡ፣ በጣም ጥቂት ጓደኛ ያላቸው ፣ ቁጥብ ፣ ረጋያሉና ገለልተኛ በመሆናቸው በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ፍዝ ናቸው (Lightbown & Spada2006) Dornyei.(2005)፤ (Browen 2000፤ 1994)፡፡

በቋንቋ መማር ሂደት ተሳታፊነትና ጭምትነት ባህርይ መካከል ሁለት ዓይነት ግምት መኖሩን Griffiths. (1991b) ይገልፃሉ፡፡ የመጀመሪያው ግምት ተሳታፊነት የሰብዕና ባህሪ ያላቸው ተማሪዎች ከብዙዎች ጋር መግባባት ስለሚችሉ ሰፊ ግብዓት የማግኘት፣ በቋንቋ የመናገር፣ የመግባባት፣ የመጠየቅ፣ የመመለስ፣ አስተያየት የመስጠትና የመወያየት እድሉ ሰፊ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ መላምት ውጤት የሚያሳየው ማህበራዊ(ግቡቡ) የሆኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የበለጠ የመሳተፍ ዕድሉ አላቸው፡፡ ከዚህ የተነሳ ተሳታፊነት በክፍል ውስጥ ለሚደረገው ለቋንቋ ትምህርት ተሳትፎ አዎንታዊ ተፅዕኖ አለው (Williams,1971)፡፡ ሁለተኛው መላምት ጭምትነት ያላቸው ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት ያላቸው ዕውቀት ከፍተኛ በመሆኑ የበለጠ ይሰራሉ፡፡ የዚህ መላምት እይታው ጭምት የሆኑ ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርት በሚያገኙት ስኬት ይደሰታሉ፡፡ ይሁን እንጂ በክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው፡፡ ለራሳቸው ውጤታማ የሚሆኑት በማንበብና በመፃፍ መሆኑን Griffiths (1991b) ገልፀዋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ Lee. (2005) ተሳታፊነት ያላቸው ተማሪዎች ጭምት ከሆኑት ይልቅ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ ምክንያቱም ጭምት የሆኑ ተማሪዎች ከተወሰኑት ጋር ብቻ ግንኙነት ስላላቸው በክፍል ውስጥ ለመጠየቅም ሆነ ለመመለስ ፍላጎት የላቸውም፡፡ በመሆኑም ጭምት የሆኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፏቸው ዝቅተኛ ነው (Barrett & Connot 1986) ፡፡ በሌላ በኩል Williams. (1971) እንደገለፁት ጭምት የሆኑ ተማሪዎች ብዙ መገንዘብ የሚችሉ ቢሆኑም በክፍል ውስጥ ባላቸው አፈፃፀም ተሳታፊነት ባህር ካላቸው ተማሪዎች ዝቅተኛ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ Griffiths. (1991b) እንደገለፁት ጭምት ተማሪዎች የራሳቸውን የግል መረጃ ለማቅረብ፣ ከመምህራንና ከጓደኞቻቸው ለሚቀርበው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት ፈቃደኛ አይሆኑም፡፡ ከዚህ የተነሳ ብዙ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት አስቸጋሪ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ኃላፊነት መቀበል በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱት ከሰብዕና አይነቶች አንዱ ነው (Browen, 2000) ፡፡ Beebe. (1983) እንዳብራሩት በቋንቋ መማር ሂደት ኃላፊነት የሚቀበሉ ተማሪዎች የማያመነቱ ቋንቋን ለመጠቀም ፍላጎት ያላቸው፣ ለስህተት ቦታ የሌላቸውና ከመናገር በፊት ብዙ ለማሰላሰል የማይፈልጉ በመሆናቸው ለመጠየቅ፣ ለመመለስ፣ ለመወያየትና አስተያየት ለመሰጠት ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ኃላፊነት መቀበል በክፍል ውስጥ ተሳትፎ አዎንታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

በተጨማሪም Beebe. (1983) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለመሳተፍ ካላቸው ፍርሃት ለምሳሌ ከትምህርት ውጤት፣ በፈተና መውደቅ፣ ከመምህራን ወቀሳ፣ ከጓደኞቻቸው ማሽሟጠጥና ቅጣት ጋር በማያያዝ በክፍል ውስጥ ለመሳተፍ ኃላፊነት መቀበል የማይፈልጉ መሆናቸውን ይገልፃሉ፡፡ ይህ ደግሞ በተማሪ ክፍል ውስጥ ተሳትፎ አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳለው ከላይ የተጠቀሱ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡

ለራስ ከበሬታ መስጠት አንዱ የሰብዕና ባህርይ ነው፡፡ ይህ የሰብዕና ባህርይ ያላቸው ተማሪዎች በክፍል ውሰጥ ተሳትፎ ለማድረግ ካላቸው ፍላጎት አንፃር በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ በማድረስ ተሳትፎን ሊገድቡ እንደሚችሉ Morsen & Tomosnee (1975) ይገልፃሉ፡፡

Morsen & Tomosnee (1975) እንዳብራሩት በከፍተኛ ደረጃ ለራስ ከበሬታ መስጠት ከግለሰቡ ቋንቋ ችሎታ ጋር ግንኙነት ያለ ሲሆን የሚገለፀውም ግለሰቡ በራስ መተማመን ኖሮት ራሱ አስፈላጊ ሰው መሆኑን በማመን ለራሱ ከሚሰጠው ደረጃ አንፃር ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ከፍተኛ ከሆነ በቋንቋ ለመግባባት፣ ለመጠየቅ፣ ለመወያየት ያላቸው ፍላጎት ይጨምራል፡፡ በአንፃሩ ደግሞ በውስጣቸው ያለው ፍርሃት ይቀንሳል፡፡ ዝቅተኛ ግምት ለራሳቸው የሚሰጡ ከሆነ ለክፍል ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ ይሆናል (Williams 1971)፡፡ በተመሳሳይ Browen, (2000) ተማሪዎች ራሳቸውን በበታችነት ስሜት የሚያዩ ከሆነ ተሳትፎ እንደማያደርጉ ይገልፃሉ፡፡

ይህንን ሀሳብ በማጠቃለል Browen, (2000) ተሳታፊነትን ሀላፊነት ከመቀበል ጋር፣ ጭምትነትን ደግሞ ለራስ ከበረታ መስጠት ጋር አያይዘው ያዩታል፡፡ በመሆኑም የሰብዕና አይነቶች በቋንቋ መማር ሂደት በክፍል ውሰጥ ተሳትፎ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተግዳሮት ሊያደርሱ እንደሚችሉ መረዳት የሚቻል ሲሆን በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ የሚገኙ ተማሪዎች ለዚህ ጉዳይ በከፍተኛ ሁኔታ ተጋላጮች ናቸው፡፡

## 2.2.1.4 ጭንቀት

ጭንቀት በቋንቋ ትምህርት በተማሪዎች ላይ ስሜታዊ ተግዳሮት ከሚሆኑት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ Browen, (2000) ፤ Spielbrger. (1983)ን ጠቅሰው ጭንቀት በቀላሉ ሊገለፅ የማይችል ውጥረት፣ ፍርሃት፣ ስጋትና ንዴት ስሜት ተዳምረው የሚፈጥሩት አፋጣኝ የነርቭ ሥርዓት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ከዚህ ጋር በማያያዝ ጭንቀት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተግዳሮት ያለውና አጠቃላይ አዕምሮአዊ ተግባር ማለትም መማርን ማነሳሳት እና ማመቻቸት እንዲሁም ማበላሸት ወይም መበጥበጥ የሚችል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

በተመሳሳይ ጭንቀት ስሜታዊ ተግዳሮት በሰዎች ላይ የሚፈጥር ሲሆን የሰዎች ትኩረት እና ግንዛቤ ላይ ተግዳሮት የሚሆኑና በቋንቋ ትምህርት ያለውን ቁርጠኝነት የሚያሳጣ ነው (Spielbrger. 1983)፡፡ የተለያዩ የጭንቀት አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም ባህርያዊ(trait) ጭንቀት፣ ጊዜያዊ (state) ጭንቀት እና ሁኔታዊ(situational) ጭንቀት ናቸው (ስካቨል 1978)፡፡ ባህሪያዊ (trait anxiety) ጭንቀት ግላዊ እና በተወሰኑ ሰዎች በተለያዩ ጉዳዮች አንፃር የሚከሰት ጭንቀት ነው፡፡ Browen, (1994) እንደገለፀው ባህሪያዊ ጭንቀት በጣም

የተለመደና ቋሚ የሆነ በቀላሉ ለመተው የማይቻል የጭንቀት አይነት ነው፡፡ በአንፃሩ ጊዜያዊ (state anxiety) ጭንቀት ሰዎች በመጥፎ ሁኔታ ውስጥ በመግባት ካላቸው ስጋትና ፍርሃት አንፃር የሚፈጠር ጭንቀት ነው (Spielbrger. 1983)፡፡ ባህርያዊ ጭንቀት በሰዎች ባህሪ በቀጥታ የሚገለፅ አይደለም፤ ነገር ግን በተደጋጋሚ ከሚታየው ጭንቀት አንፃር ግለሰቦች ከሚሰጡት ግላዊ ግምገማ አንፃር ባህሪያዊ ጭንቀት ቋሚ ሰብዕና ልዩነት ሊያሳይ ይችላል፡፡ በሌላ በኩል ጊዜያዊ ጭንቀት ጊዜያዊና በዚያች ጊዜ ከሚከሰቱ ነገሮች ወይም ሁኔታዎች ጋር የተያያዘ ነው፡፡ ለምሳሌ ፈተና ሲፈተኑ በተማሪዎች የሚታይ የጭንቀት ስሜት በጊዜያዊ ጭንቀት ሊመደብ ይችላል፡፡ አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ ባህርያዊ ጭንቀት ያላቸው ተማሪዎች ካለው ሁኔታ አንፃር ከፍተኛ ጊዜያዊ ጭንቀት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡ በመሆኑም ባህርያዊና ጊዜያዊ ጭንቀት በውስጣቸው ጥብቅ ትስስር አላቸው፡፡

ሶስተኛው የጭንቀት አይነት ሁኔታዊ (situation specific anxity) ጭንቀት ነው፡፡ Petres. (1978) እንደገለፁት ሁኔታዊ ጭንቀት ከጊዜያዊ ጭንቀት ጋር የሚመሳሰል ሲሆን በሁኔታ ብቻ ተወስኖ የሚቀጥል ሳይሆን በተወሰነ ሁኔታ ለብዙ ጊዜ ቋሚ ሆኖ የሚቆይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ሲታይ ሁኔታዊ ጭንቀት ከባህርያዊና ከጊዜያዊ ጭንቀት የተለየና አንዱ በአንድ በተለየ ጉዳይ ላይ ተመስርቶ በሁኔታዊ ጭንቀት ውስጥ ይገኛል፡፡ሁኔታዊ ጭንቀት የተለያዩ ሁኔታዎችንና ድርጊቶች መሰረት በማድርግ የሚከሰት ነው፡፡ የዚህ አይነት ጭንቀት በማህበራዊ ንግግር፣ በፈተና ወይም በክፍል ተሳትፎ ላይ የሚታይ ጭንቀት አይነት ነው Spielbrger 1983)፡፡

ጭንቀት ተማሪዎች አዲስ ነገር እንዳያስተውሉ ዕውቀትና ክሂል እንዳያዳብሩ ትምህርቱን በስርዓት እንዳይከታተሉ ያደርጋል (Spielbrger 1983)፡፡ በሌላ በኩል Secavile. (1978) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በግላቸው ተሳትፎ እንዲያደርጉ በማስቻል አዎንታዊ ተግዳሮት ሊኖር እንደሚችል ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ጭንቀት አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተግሮት ሊኖረው እንደሚችል ከላይ ከተገለፁ ፀሐፊዎች ገለፃ መረዳት ይቻላል፡፡የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችም የዚሁ አካል ስለሆኑ ከለሎቹ ለይቶ ማየት አይቻልም፡፡

#### 2.2.1.5 ዖታ

የተማሪዎች ፆታ ልዩነት የክፍል ተሳትፎን ከሚገድቡ ተግዳሮቶች አንዱ እንደሆነ ጥናቶች ይጠቁማሉ (Pearson & West 1991፤Petres 2000)፡፡ በጥናታቸው እንዳረጋገጡት በክፍል ውስጥ ባላቸው ተሳትፎ ወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች የበለጠ ተሳታፊ እንደሆኑ ይገልፃሉ፡፡ Tannen (1992) እንዳብራሩት ሴት ተማሪዎች ልምምድ የሚያደርጉ ከሆነ ተሳታፊ ይሆናሉ ሲሉ Pearson & West (1991) ከሴት ተማሪዎች ይልቅ ወንድ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በግላቸውም ሆነ በአጠቃላይ ለተሳትፎ ያላቸው ተነሳሽነት ከፍተኛ መሆኑን ይገልፃሉ፡፡ Williams (1990) በቺሊ ውስጥ ባካሄዱት ጥናታቸው ሴት ተማሪዎች ሴት መምህራን ሲያስተምሯቸው በክፍል ውስጥ ለመሳተፍ ያላቸው ፍላጎት ከፍተኛ ሲሆን ወንድ መምህራን ሲያስተምሯቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ እንደሆነ ይገልፃሉ፡፡ በመሆኑም ፆታ በተማሪ ክፍል ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖ እንደሚያስከትል Pearson & West (1991) ያስረዳሉ፡፡

### 2.2.1.6 የተማሪዎች ቋንቋ ደረጃ

ቋንቋ በመማር ማስተማር ሂደት የተማሪዎች ቋንቋ ደረጃ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን ከሚወስኑት ተፅዕኖዎች አንዱ ነው፡፡ ተማሪዎች አፋቸውን የፈቱበት ቋንቋ ትምህርቱ ከሚሰጥበት ወይም ከታላሚ ቋንቋ የተለየ ከሆነ በሚማሩት ቋንቋ ትምህርት ላይ ጫና ይፈጥራል (Li & Liu 2011) ፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች የታላሚ ቋንቋ እውቀት ከሌላቸው በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ስህተት ይፈጠራል በሚል ስጋት በክፍል ውስጥ ለመወያየት፣ ሀሳብ ለመግለፅ፣ ለመጠየቅም ሆነ ለመመለስ አይፈልጉም፡፡ ስለሆነም ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የቋንቋ ትምህርቱን ለመማር ትምህርቱ የሚሰጥበት ቋንቋ እውቀትና የመጠቀም ችሎታ ሊኖራቸው ይገባል (Namona. 2008)፡፡በተመሳሳይ Li & Liu (2011) እንደገለፁት ተማሪዎች ቋንቋን ሲማሩ በክፍል ውስጥ ከመምህራቸው የሚሰጣቸውን ተግባራት ለመፈፀም የሚችሉት በቋንቋው ችሎታ ሲኖራቸው ነው፡፡

በመሆኑም መምህሩ ሁል ጊዜ ሲያስተምር የተማሪዎችን የቋንቋ ደረጃ መፈተሽ አለበት፡፡ በዚህም መምህሩ ተማሪዎች ቋንቋውን ምን ያህል እንደተማሩ ለመገምገም ይረዳዋል፡፡በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ የተጠኑ ጥናቶች እንደሚገልፁት የተማሪዎች

አፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት (language interference) በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ ተግዳሮት በማድረግ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን ሊገድብ እንደሚችል ያስረዳሉ (Lightbown & Spada 2006) ፡፡ በተመሳሳይ Browen. (2000) እንደገለፁት የተማሪዎች አፍ መፍቻ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድራል፡፡ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋን የሚማሩበት ሁኔታ አንደኛ ቋንቋ ከለመዱበት ሂደት የተለየ በመሆኑ በታላሚው የቋንቋ ትምህርት አቀባበል ላይ ተግዳሮት አለው፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች የቋንቋ ደረጃቸው ዝቅ ያሉ ከሆነ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ስህተት እንሰራለን ብለው ይፈራሉ (Browen. 2000) ፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለመናገር አይፈልጉም፣ ጥያቄ አይጠይቁም፣ የራሳቸውን ሀሳብ አይገልፁም፣ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ አያደርጉም፡፡ ከዚህ አንፃር በትምህርቱ ያላቸው አፈፃፀም ዝቅተኛ ይሆናል (Namene. 2008)፡፡በሌላ በኩል (Namene 2008) እንደገለፁት ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋ ሲማሩ ከተመሳሳይ ቋንቋ ተናጋሪ ቤተሰብ የመጡ ከሆነና ተመሳሳይ ፊደልና ድምፆች የሚጠቀሙ ከሆነ ትምህርቱ ቀላል ይሆናል፡፡ ተማሪዎቹም ትምህርቱን በቀላሉ ሊማሩትና ሊረዱት ይችላሉ፡፡

## 2.2.2 የመምህሩ ተግዳሮት

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት በተማሪ ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ የመምህሩ ማስተማር ዘዴና የመምህሩ ባህርይ በተማሪ ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖ በማሳደር የተማሪ ክፍል ተሳትፎን ሊወስን እንደሚችል Li, Thi,Mai.(2011) ይገልፃሉ፡፡

### 2.2.2.1 የማስተማሪያ ዘዴ

ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱት ጉዳዮች መካከል አንዱ ትምህርቱ የሚቀርብበት የማስተማሪያ ዘዴ ነው፡፡ መምህራን እንደትምህርቱ ይዘት ተገቢ የማስተማሪያ ዘዴ የማይጠቀሙ ከሆነ በተማሪዎች የትምህርት አቀባበልም ሆነ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ውስንነት ሊከሰት እንደሚችል Dbise (1981) ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መምህራን ረጅም ጊዜ መምህር ተኮር በሆነ የገለፃ ዘዴ

የሚያስተምሩ ከሆነ ተማሪዎች እንዲሳተፉ እድል ስለማይሰጥ የመማር ማስተማሩ ሂደት እንደሚጎዳ እና ተማሪዎችም ትምህርቱን ተምረዋሉ ለማለት እንደማያስችል Liu & Jaksen .(2008) & Dbise (1981) ገልፀዋል፡፡

በተመሳሳይ በድሩ (1994) እንደሚያስረዱት በተማሪ አሳታፊ የማስተማር ዘዴ መምህሩ የመማር ሂደት አመቻች የሆነበትና በተማሪዎች መካከል የእርስበርስ ግንኙነት የተጠናከረበት ነው፡፡ተማሪዎች በሚና ጨዋታ፣ በቡድን ወይይት፣ በመስክ ስራ፣ በማስመሰል፣ በግል ጥናት የሚሳተፉ ሲሆን ለተማሪ-ተማሪና ለተማሪ-መምህር መስተጋብር ትኩረት ይሰጣል፡፡ በዚህ ዘዴ ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊዎችና ለመማር ኃላፊነት የሚወስዱ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ መምህሩ የሚከተለው የማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን ተሳትፎ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ በሆነ መልኩ ተፅዕኖ ሊያደርስበት ይችላል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን ውጤታማ የሚባለውና ትኩረት የተሰጠው በክፍል ተግባራት ላይ ተማሪዎች በንቃት እንዲሳተፉ የሚያደርገው ተማሪ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን በድሩ (1994) ይገልፃል፡፡

### 2.2.2.2 የመምህሩ ባህሪይ

በቋንቋ ማስተማር ሂደት ከመምህሩ ባህርይ በሚመጣ ተፅዕኖ የተማሪ ክፍል ውስጥ ተሳትፎን ሊወስን እንደሚችል Bradine, (1986) ይገልፃሉ፡፡ መምህራን በክፍል ውስጥ የክፍል ፀጥታ የማያስጠብቁ፣ የሚቀልዱ፣ ተማሪዎችን የበታችነት ስሜት ውስጥ እንዲገቡ የሚያደርጉ ወይም አሳንሰው የሚያዩና የሚተቹ ከሆነ ተማሪዎች የክፍል ተሳትፎ ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት ዝቅተኛ ይሆናል (Yulise 1976)፡፡

በተጨማሪም መምህሩ አስፀያፊ ባህርይ ካለው ወይም ተማሪዎችን የሚሳደብ፣ ያታዊ ትንኮሳ የሚፈፅምና መጥፎ ሰብዕና ያለው ከሆነ በመማር ማስተማርና በክፍል ውስጥ ተማሪ ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ በማሳደር የክፍል ተሳትፎ የሚወስን መሆኑን Bradine (1986) አመላክቷል፡፡ ከዚህ ጋር አያይዘው መምህሩ የሚቆጣ፣ የተማሪ ሰሜት የማይረዳ፣ በጎ የማያስብ፣ ግትር፣ የሚያሸማቅቅ፣ ተማሪዎችን ዝቅ አድርጎ የሚመለከት፣ ተማሪዎችን

ወደራሱ የማያቀርብ፣ ለተማሪ ፊት የማይሰጥ ወይም አምባገነን ከሆነ ተማሪዎች የክፍል ተሳትፎ ለማድረግ ፈቃደኛ አይሆኑም (Bradine 1986)፡፡

## 2.2.3 የመማር እና የማስተማር ሁኔታዎች

የመማር ማስተማር ሁኔታ በተማሪ ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱት ጉዳዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ትምህርቱን ተረጋግተው በሰከነ መልክ እንዲማሩ የመማሪያ ክፍል አካላዊ ሁኔታ እና የክፍል ውስጥ አየር ሁኔታ ምቹ መሆን ይኖርበታል፡፡ በመሆኑም መማር እና ማስተማር የሚካሄድበት ሁኔታ በተማሪ ክፍል ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖ ያደርሳል (Li, Thi, Mai 2011) ፡፡

### 2.2.3.1 የክፍል ውስጥ ተጨባጭ ሁኔታ

የክፍል ውስጥ ተጨባጭ ሁኔታ የሚባሉት የተማሪ ቁጥር (class size) ፣ ጠረጴዛ፣ ወንበር፣ የክፍል ውስጥ ብርሃንና ሠሌዳ የሚያካትት ነው፡፡ የእነዚህ ነገሮች ምቹ መሆን ወይም አለመሆን የክፍል ተሳትፎን አሉታዊ ወይም አዎንታዊ በሆነ መንገድ ሊወስኑ እንደሚችሉ Li, Thi, Mai (2011) ይገልፃል፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት በአንድ ክፍል የሚገኙ የተማሪ ቁጥር ከተማሪዎች ስኬት እና ተሳትፎ ጋር በቀጥታ ግንኙነት እንዳለው በርካታ ፀሐፍት ገልፀዋል፡፡ Rocca, (2009)፣ እንዳስረዳው የተማሪ ቁጥር ከበዛ ውጤታማ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት ማካሄድ አይቻልም፡፡ ምክንያቱም መምህሩ የክፍል ስራም ሆነ የቤት ስራ በማሰራት ተማሪዎችን ማሳተፍ አይችልም፡፡ የተማሪ ቁጥር አነስተኛ በሚሆንበት ጊዜ ግን መምህሩ ተማሪዎችን በበለጠ ማሳተፍና በተናጠል የሚያከናውኗቸውን ተግባራት እየተከታተለ ማስራት ይችላል፡፡

Yulise (1976) እንደሚያብራሩት ደግሞ የተማሪዎች ቁጥር ሲበዛ እያንዳንዱ ተማሪ በተናጠል ተገቢ ቁጥጥርና ድጋፍ አይደረግለትም፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት ላይ ጥላቻ ሊያሳድሩ ይችላሉ፡፡ ስለሆነም ተማሪዎችን የበለጠ ለማሳተፍ በአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ መገኘት ያለበት የተማሪ ቁጥር ከሃያ እስከ አርባ ቢሆን እንደሚመረጥ Yulise (1976) ይጠቁማሉ፡፡ በተመሳሳይ Rocca. (2009) መምህር

ተማሪዎችን በሚገባ ለይቶ እንዲያሳትፋቸው በአንድ ክፍል ውስጥ ሊኖር የሚገባው የተማሪ ቁጥር ከአርባ እስከ ሃምሳ መሆን እንዳለበት ይገልፃሉ፡፡

Davies (1981) እንደገለፁት ደግሞ የተማሪዎች ቁጥር ይህን ያህል ነው ብሎ ቁርጥ ያለ መልስ መስጠት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም ቁጥሩ እንደየሁኔታው ይወሰናል፡፡ በአጠቃላይ ግን ብዙ ቁጥር ካለው ክፍል ይልቅ ጥቂት ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተሻለ ተሳትፎ ይኖራቸዋል፡፡

በተጨማሪም Li, Thi, Mai. (2011) ፤ Harmer. (2001) ን ጠቅሰው የመማሪያ ክፍል ውስጥ ሁኔታ በተማሪ መማርና በትምህርቱ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድር እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ጥሩ ያልሆነ የክፍል ውሰጥ ሁኔታ ተማሪዎች ተነሳስተው እንዳይማሩ ያደርጋል፡፡ ብዙ የተማሪ ቁጥር ባለበት ክፍል ለመማር ማስተማር ምቹ ባለመሆኑ በመምህሩና በተማሪ መካከል ያለው ግንኙነትን የሚቀንስና ተነሳሽነትን የሚያሳጣ መሆኑን Li, Thi, Mai. (2011) ገልፀዋል፡፡

## 2.2.3.2 የክፍል ውስጥ አየር ሁኔታ

የክፍል ውስጥ አየር ሁኔታ የሚገለፀው ከመማሪያ አከባቢ ወይም ከወቅታዊ አየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ ነው፡፡ የትምህርት አከባቢ አየር በተማሪዎች መማርና በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ በጎ ወይም በጎ ያልሆነ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡ የአከባቢ አየር የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ አቀማመጥንም ይወስናል (Li, Thi, Mai, 2011) ፡፡

በአጠቃለይ ተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ሲማሩ የክፍል ተሳትፎ ወሳኝ በመሆኑ ለተማሪዎችና ለመምህራን ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለውና የተማሪ ክፍል ተሳትፎ ከተማሪ፣ ከመምህርና ከመማር ማስተማር ሁኔታ አንፃር ሊወሰን እንደሚችል ከላይ ከተገለፁ ፀሀፍት ገለፃ መረዳት ይቻላል፡፡

### 2.2.3.3 የተዛማጅ ጥናት ቅኝት

አጥኝዋ በዚህ ክፍል ውስጥ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢ የሆኑና ከዚህ ጥናት ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ዝምድና ያላቸው ቀደምት ጥናቶችን በመቃኘት ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ለመግለፅ የሚሞከርበት ክፍል ነው፡፡ በጥናቱ ትኩረት የሚደረግባቸው ነጥቦች ከርዕስ ፣ ከዓላማ ፣ ከአጠናን ዘዴ ፣ሲሆን፤ ከእነዚህ ነጥቦች አንፃር የሚከተሉት ስራዎች ታይተዋል።የተማሪ ተሳትፎ አስመልክቶ የተጠኑ ጥናቶች ስንመለከት

ፋሲል (2002) የተማሪ ክፍል ተሳትፎ ላይ ክፍተት በመኖሩ ሊተኮር እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡ ሆኖም ዋና ትኩረታቸው በተማሪ ክፍል ተሳትፎና የትምህርት ውጤት ተዛምዶ ላይ ነው፡፡

ስፈራሽ (2002) በፅሁፍ መጠይቅና ምልከታ ባገኙት መረጃ መሰረት የክፍል ተሳትፎ ችግር እንዳለ እና መምህራን በቂ ዝግጅት እንደማያደርጉ ይገልፃሉ ፡፡ የክፍል ተሳትፎን በተመለከተ ተግዳሮቶቹ ተተንትኖ መለየት ያላለቀና ገና ጥናት የሚፈልግ ጉዳይ በመሆኑና በአጠቃላይ እስካሁን ድረስ የተካሄዱ ጥናቶች ለጉዳዩ ዘላቂ መፍትሂ ባለማግኘታቸው ጥናቱ በስፋትና በጥልቀት ያልተጠና በመሆኑ ተጨማሪ ጥናት የሚጋብዝ ነው፡፡ ስለዚህም አጥኝዋ ያገኘቻቸው ጥናቶች ተሳትፎን ከውጤት ተዛምዶና ከትምህርት አቀራረብ አንፃር ብቻ የመረመሩ በመሆኑና ተግዳሮቶችን ያልተመለከቱና ያልተነተኑ በመሆኑ፣ አጥኝዋ የመረጠችው ርዕስ ከሌሎቹ ጥናቶች ይለየዋል ፡፡

በተጨማሪም በክፍል ተሳትፎ ላይ እነዚህና ሌሎች መሰል ጥናቶች የተካሄዱ ቢሆንም ችግሩ እየተባባሰ እንጅ እየተቀረፈ እንዳልሄደ የተለያዩ ምሁራን ከሰነዘሩት ሀሳብና ከጥናት ውጤቶች መረጃ ባለመገኘቱ የተማሪዎች የክፍል ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮት መተንተን ችግሩን ለመቅረፍ ያስችላል የሚል እምነት አሳድሯል ፡፡ ከዚህ አንፃር አጥኝዋ ይህንን ክፍተት ለመሙላት ተማሪዎች ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መተንተን በማለት ወደ ጥናት ለመግባት ተነሳስታለች፡፡

በተጨማሪ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መተንተን የዚህ ጥናት አብይ ትኩረት ነው፡፡ይህ ጥናት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ

የሚማሩ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መተንተን ነው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት የጥናት አቅራቢዎች ባጠኑት ላይ በመመርኮዝ የተገኙትን መልካም ተሞክሮዎችንና ሥራዎችን በመውሰድ እንድሁም የታዩትን ክፍተቶችን በመሙላት በጥልቀት ጥናት በማድረግ ችግሮችንና መፍትሄዎቻቸውን ለመጠቆም ተሞክሯል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## 3. የጥናቱ ንድፊ እና አካሄድ

### 3.1 የጥናቱ ንድፊ

የዚህ ጥናት ትኩረት አማርኛን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ የሚማሩ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎአቸውን የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መተንተን ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ጥናቱ የሚከተለው መጠናዊ ምርምር ዘዴ ሲሆን አቀራረቡም ገላጭ ነው፡፡

### 3.2 የጥናቱ አካላይ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በደቡብ ብሔርብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግስት በዳውሮ ዞን ካሉት አሥራ አምስት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ዉስጥ በሦስት ትምህርት ቤቶች ማለትም በታርጫ ፣ቱሪ እና ማረሚያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በ2011 የትምህርት ዘመን በዘጠነኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ትምህርት የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መተንተን ነው፡፡ በጥናቱ የተሳተፉት በታርጫ ፣ቱሪ እና ማረሚያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በ2011 የትምህርት ዘመን በዘጠነኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎችና መምህራን ናቸው፡፡ በዘጠነኛ ክፍል ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ተማሪዎች በፅሁፍ መጠይቅ ለማካተት አስቸጋሪ ስለሚሆን በቀላል ዕጣ ናሙና ከ600 ተማሪዎች መካከል 91 ወንድ እና 80 ሴት በድምሩ 171 ተማሪዎች ከዘጠኝ ክፍል በጥናቱ ውስጥ ተካተዋሉ፡፡ የሴትና የወንድ ተማሪዎች ቁጥራቸው የተለያየ የሆነበት ምክንያት በቀላል ዕጣ ናሙና ዘዴ የተመረጡ ስለሆነና ቁጥራቸውም ያነሰው አስፈላግውን መረጃ ለማሰባሰብ አመቺ ስለሆነ ነው፡፡

### 3.3 የናሙና አመራረጥ ዘዴ

#### 3.3.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

አጥኝዋ የምትሰራበት ትምህርት ቤት ታርጫ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን ቀሪዎች ቱሪ እና ማረሚያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች ከአጎራባች ወረዳዎች በአመቺ ንሞና ዘዴ ተመርጧል ምክንያቱም እነዚህ ትምህርት ቤቶች

የተመረጡት ጊዜንና ጉልበትን እንድሁም ደግሞ በጀትን በአግባቡ ለመጠቀም ተፈልጎ ተመርጧል፡፡

### 3.3.2 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በትምህርት ቤቱ ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ቀደም ሲል የሚሰጠዉ የአማርኛ ቋንቋ ቀርቶ የብሔረሰብ ቋንቋ (ዳዉሮኛ) በምትኩ የሚሰጥ ስለሆነ የክፍል ዉስጥ ምልከታን በብቃት ማግኘት ስለማይቻል በጥናቱ አይካተቱም  የ9ኛ እና 10ኛ ክፍል ግን በሣምንት ሁለት ጊዜ ስለሚሰጥ ማግኘት ይቻላል፡፡ ይሁንና የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የብሄራዊ ፈተና የሚፈተኑ ከመሆናቸው አንፃር በቂ መረጃ ላይገኝ ይችላል በሚል ግምት ዘጠነኛ ክፍል  በዓላማ ተኮር ንሞና ተመርጧል፡፡

### 3.3.3 የመምህራንና ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

መምህራንን በተመለከተ በሦስቱም ትምህርት ቤቶች ዘጠነኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን አራት በመሆናቸው በጠቅላይ ንሞና ዘዴ ሁሉም በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ ከዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በእያንዳንዱ ክፍል ከ60-70 ካሉት ተማሪዎች ከዘጠኝ ክፍል በአጠቃላይ 600 ተማሪዎች መካከል 171 ተማሪዎችን በቀላል ዕጣ ናሙና ተመርጧል፡፡ ይህም የሆነው መምህራን በሚያስተምሯቸው የመማሪያ ክፍሎች ያለውን የክፍል ውስጥ ተማሪ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮት ለመመልከት አመቺ ስለሆነና በዚህ መንገድ የተገኘዉ መረጃ አስተማማኝ ስለሚሆን ነው፡፡

## 3.4. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በዚህ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ አግልግሎት ላይ የዋሉት ዘዴዎች የፅሁፍ መጠይቅ፣ ምልከታና ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.4.1. የፅሁፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት የተመረጠበት ምክንያት ተጠኝዎች ነፃ ሆነው ያላቸውን አመለካከት እና አስተያየት በትክክል እንዲሰጡ ያስችላል በሚል ግምት ነው፡፡ ያለው (2004) እንደገለፁት የጽሁፍ መጠይቅ አስተማማኝና ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል እንዲሁም መረጃ

ለመሰብሰብ እና ለማደራጀት ቀላል የሆነ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡ መጠይቁም የተዘጋጀው ለመምህራንና ለተመረጡ ተማሪዎች ነው በመሆኑም የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመለየት ከጥናቱ አላማና በክለሳ ድርሳናት ከቀርቡት ነጥቦች አንፃር ሰላሳ ዝግ(Close ended)ና ሁለት ክፍት(open ended)ጥያቄዎች ከስፍራሽ (2002)፣ Geeren, (2008) ተወስዷል፡፡ Geeren መጠይቅ በክፍል ተሳትፎ ላይ ጫና በሚፈጥሩት ተግዳሮት ላይ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ሲሆን የስፍራሽ መጠይቅ ተሳትፎ ላይ ስለሚያተኩር በከፊል ከጥናቱ ጋር ስለሚገናኝ ነው፡፡ የቀረበው መጠይቅ አመለካከት፣ ጭንቀት፣ ተነሳሽነት፣ ሰብዕና፣ ፆታ፣ የተማሪ ቋንቋ፣ የትምህርት አቀራረብ፣ የመምህሩ ባህርይ እና የመማር ማስተማር ሁኔታዎችን ያካትታል፡፡

በመጠይቁ ለእያንዳንዱ ጥያቄ መልስ መወሰኛ አምስት ነጥብ መልስ መለኪያዎች ቀርበዋል፡፡ ይኸውም ከከፍተኛ ወደ ዝቅተኛ በጣም እስማማለሁ (5) እስማማለሁ (4) ለመወሰን ያስቸግረኛል (3) አልስማማም (2) በጣም አልስማማም (1) የሚሉ አማራጮች ናቸው፡፡ የመጠይቁን አስተማማኝነትና ተገቢነት ይበልጥ ለማረጋገጥ ጥያቄዎቹ የተዘጋጁት በአጥኝዋ ሲሆን በአማካሪ እና በስነ ልቦና መምህራን ተገምግሞ በስራ ላይ ውለዋል፡፡

### 3.4.2. ምልከታ

በመረጃ መሰብሰቢያነት የተመረጠበት ምክንያት በመማር ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ ሲማሩ ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመለየት፣ በዝርዝር ለማስተዋል እና ለጥናቱ ጠቃሚ መረጃ ለመሰብሰብ ስለሚያስችል ነው፡፡በተጠኝ ተማሪዎች አጥኝዋ ምልከታ የጀመረችው ከመጋቢት 13/07/2011 ጀምሮ ለሦስት ተከታታይ ሣምንት መምህራን በሚገቡበትን አራት ክፍል  እያንዳንዱን ክፍል ሦስት ጊዜ በጠቅላላው አስራ ሁለት ጊዜ ምልከታ ተደርጓል፡፡

በመሆኑም አጥኝዋ የክፍል ተሳትፎን በተመለከተ ፋሲል (2002) Petress (2000)& Edward (2006)ን ማብራሪያዎች ጠቅሰው የተጠቀመበትንና ስፍራሽ (2002) የተማሪ

ተሳትፎ ለመለካት የተጠቀመችበትን የምልከታ ማመሳከሪያ ቅፅ (observation checklist) ከጥናቱ አላማና ክለሳ ድርሳናት አንፃር ማሻሻያ በማድረግ ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል፡፡

በተዘጋጀው ማመሳከሪያ ቅጽ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ከሚያስተምሯቸው ክፍሎች ከእያንዳንዳቸው በቀላል ዕጣ ናሙና በተመረጡት አራት የመማሪያ ክፍሎች በአንዱ የመማሪያ ክፍል ውስጥ ሶስት ሶስት ጊዜ በአጠቃላይ አስራ ሁለት ጊዜ የክፍል ምልከታ ተካሂዷል፡፡

የማመሳከሪያ ቅፁ የተሞላው ዝርዝር ባህርያቱን መሰረት በማድረግ ባህሪያት ካሉ ‹‹አዎን›› በሚለው የስምምነት መግለጫ ስር ‹‹✓›› ምልክት በማድረግና ከሌለ ደግሞ ‹‹አይደለም›› በሚል መግለጫ ስር ‹‹✓›› በማድርግ መረጃው ተሰብስቧል፡፡ አባሪ "ለ"ን ይመልከቱ ፡፡

### 3.4.3. ቃለ መጠይቅ

ቃለ መጠይቅ የተመረጠው በጽሁፍ መጠይቅ እና በክፍል ውስጥ ምልከታ የተገኘውን መረጃ ለማጠናከር ነው፡፡ አጥኚዋ ጥናቱን በሚታካሂድበት ጊዜ አይነታዊ መረጃ ከመተንተኑ በፊት በክፍል ውስጥ የተማሪ ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት የሚሆኑ ነገሮች ምን እንደሆኑ እና በክፍል ውስጥ ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶች በቋንቋ ትምህርት የሚያሳድሩትን ተጽዕኖ በመፈተሽ ለተጠኚ ተማሪዎች እና መምህራን የፅሁፍ መጠይቅና የክፍል ምልከታ ካደረገች በኋላ በታላሚ ትምህርት ቤት ለሚያስተምሩ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ለጥናቱ ከተመረጡት ተማሪዎቸ ውስጥ በቀላል ዕጣ ናሙና በመውሰድ የተካሄደ ነዉ፡፡ ከጥናቱ አላማና በክለሳ ድርሳናት ከቀርቡት ነጥቦች አንፃር ዝግ (Close ended)ና ክፍት(open ended) ጥያቄዎች ከስፍራሽ (2002)ና Geeren, (2008) ማሻሻያ በማድረግ ተወስዷል፡፡

## 3.5 የመረጃ አደረጃጀትና አተናተን

### 3.5.1 የመረጃ አደረጃጀት

ለጥናቱ የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የፅሁፍ መጠይቅ፣ ምልከታ እና ቃለመጠይቅ ሲሆን በእነዚህ ዘዴዎች የተሰበሰበው መረጃ በሚከተለው መንገድ

ተደራጅቷል፡፡ በቅድሚያ መጠይቁ በሚገባ መሞላቱንና አለመሞላቱን የመፈተሽ ስራ ተሰርቷል፤ ከተለያዩ ክፍል በምልከታ፣ በቃል መጠይቅ እና በጽሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ በአይነት በአይነቱ ለትንታኔ በሚመች መንገድ ተደራጅቷል በመቀጠልም የተደራጁት መረጃዎች እያንዳንዱ ተሳታፊ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጠው ምላሽ ታሊ ተደርጓል፡፡

## 3.5.2 የመረጃ አተናተን

ታሊ የተደረገውን መረጃ ኤስፒ ኤስ ኤስ (spss) ስታስትክስ ነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት(One sample t-test) ቀመር ተሰልቶ ተተንትኗል፡፡ ከተለያዩ ክፍል በምልከታ ተሰበሰበው የተደራጀው መረጃ ተተንትኖ ውጤቱ በመቶኛ ተሰልቶ ቀርቧል፡፡ በሌላ በኩል በቃል መጠይቅ የተገኘውን መረጃ በአግባቡ በአይነት በአይነት ተደራጅተው ከጥናቱ አላማና ከመሪ ጥያቄዎች ጋር በማገናዘብና የተዛማጅ ፅሁፎችን መሰረት በማድረግ ትንታኔና ማብራሪያ ተሰቷል ፡፡

## ምዕራፍ አራት

# 4. የጥናት ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

## 4.1 የውጤት ትንተና

ይህ ጥናት በታርጫ ፣ በቱሪ እና ማረሚያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመፈተሽ ታስቦ የተከናወነ ሲሆን ይህንን ዓላማ ለማሳካት በጽሁፍ መጠይቅ፣ ምልከታና ቃለ መጠይቅ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በዚህ ክፍልም በፅሁፍ መጠይቅ፣ምልከታና ቃለ መጠይቅ የተሰበሰበው ውጤት ከዚህ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል ፡፡

### 4.1.1 ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ ምላሽ

በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት ትንተና፤ የሚለውን ለመፈተሽ ይረዳ ዘንድ፣ ከፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በሰንጠረዥ ተመዝግቦ በነጠላ ናሙና ቲ ቴስት ፍተሻ (One sample t-test) ተተንትኗል፡፡ ውጤቱም በሠንጠረዥ 4.1 ተመልክቷል፡፡ በተጨማሪም ከምልከታ የተገኘው መረጃ የባህሪያት ድግግሞሽ ቆጠራ በማድረግ ውጤቱም በመቶኛና በገለጻ የተተነተነ ሲሆን፣ የቃለ መጠይቅ መረጃም ተደራጅቶ በገለጻ ተተንተኖ ቀርቧል አባሪ (ሀ)፡፡

ሰንጠረዥ 4.1 ፡- በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮት በነጠላ ናሙና ቲ- ቴስት ማጠቃለያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | ተግዳሮቶች | የተሳታፊ ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የቲ ዋጋ | የነፃነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አመለካከት | 162 | 2.05 | 0.35 | 2.81 | 161 | 0.30 |
| 2 | ጭንቀት | 162 | 2.02 | 0.58 | 8.57 | 161 | 0.60 |
| 3 | ተነሳሽነት | 162 | 2.84 | 0.71 | 19.13 | 161 | 0.39 |
| 4 | ስብዕና | 162 | 1.60 | 0.00 | 3.80 | 161 | 0.50 |
| 5 | የተማሪ ቋንቋ ደረጃ | 162 | 2.01 | 0.79 | -10.72 | 161 | 0.80 |
| 6 | የትምህርት አቀራረብ | 162 | 2.00 | 0.76 | -11.02 | 161 | 0.72 |
| 7 | የመምህሩ ባህሪ | 162 | 2.97 | 0.59 | 29.71 | 161 | 0.61 |
| 8 | የመማር ማስተማር ሁኔታዎች | 162 | 2.62 | 0.65 | 22.11 | 161 | 0.61 |
| 9 | ፆታ | 162 | 2.04 | 0.79 | -13.68 | 161 | 0.48 |

የአስተማማኝነት ደረጃ $P< 0.05$

በሰንጠረዥ 4.1 እንደተመለከተው የነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶች ላይ ጉልህ ስታቲስቲካዊ ልዩነት እንዳለ የጥናቱ ትንተና ያሳያል፡፡ በሌላ በኩል በአማካይ ውጤት (Mean Ranking Order) ደረጃ መሰረት ሲታይ ስታቲስቲካዊ ልዩነት መኖሩን ያመላክታል፡፡

የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሚገድቡ ተግዳሮቶች መካከል በስፋት የታየው የመምህሩ ባህሪ ሲሆን ተግዳሮትን ለመለየት የቀረቡት ሁለት ጥያቄዎች ሲሆኑ እነሱም፡- ከአማርኛ መምህር ጋር መልካም ግንኙነት አለኝ እና መምህሩ በክፍል ውስጥ ሲያስተምር ቁጡ ነው ተብሎ በቀረበው መጠይቅ ላይ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በ"t" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"t" ዋጋ 29.71 ነው፡፡ በ161 የነፃነት ደረጃ ፣ የ"t" ሰንጠረዥ ዋጋ 1.976 ነው፡፡

የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ 29.71 ከ"t" ሰንጠረዥ ዋጋው 1.976 ጋር ሲወዳደር የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ ስለሚበልጥ የጎላ ስታቲስቲካዊ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በተመሳሳይ አማካይ ውጤቱም በደረጃ ሲቀመጥ ከፍተኛ መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም የመምህሩ ባህሪ በአንደኛ ደረጃ የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት መሆኑን ያሳያል፡፡

በመቀጠል የቀረበው ተግዳሮት ደግሞ የመማር ማስተማር ሁኔታ ሲሆን ተግዳሮትን ለመወሰን የቀረበው ጥያቄ ሦስት ሲሆን እነሱም፡- የመማሪያ ክፍል ውስጥ አቀማመጥ ተሳትፎ ለማድረግ ምቹ ነው ፤ የተማሪ ቁጥር ለክፍል ተሳትፎ ምቹ ነው እና የመማሪያ ክፍል ውስጥ ሁኔታ ለመማር ማስተማር ምቹ ነው ተብሎ በቀረበው መጠይቅ ላይ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በ"t" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"t" ዋጋ 22.11 ነው፡፡ በ161 የነፃነት ደረጃ፣ የ"t" ሰንጠረዥ ዋጋ 1.976 ነው፡፡ የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ 22.11 ከ"t" ሰንጠረዥ ዋጋው 1.976 ጋር ሲወዳደር የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ ስለሚበልጥ የጎላ ስታቲስቲካዊ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ከዚህ የምንረዳው የመማር ማስተማር ሁኔታው የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት መሆኑን ነው፡፡

በሰንጠረገፑ በተገለፀው መሰረት በሶስተኛ ደረጃ የቀረበው ተነሳሽነት ሲሆን የተግዳሮት ደረጃ ለመለየት የቀረበው ጥያቄ ሦስት ሲሆን እነሱም፡- የተሻለ ውጤት ለማግኘት ሲል በክፍል ውስጥ ተግባራት ተሳትፎ አደርጋለሁ፣ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ተሳትፎ ማድረግ ጠቀሜታ አለው እና በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሳደርግ ወይም ስናገር ስህተት ቢፈጠር ሌሎች ተማሪዎች ይስቁብኛል ብዬ እፈራለሁ ተብሎ በቀረበው መጠይቅ ላይ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በ"t" ቴስት ሲሰላ የተገኘው የ"t" ዋጋ 19.13 ነው፡፡ በ161 የነፃነት ደረጃ፣ የ"t" ሰንጠረዥ ዋጋ 1.976 ነው፡፡ የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ 19.13 ከ"t" ሰንጠረዥ ዋጋው 1.976 ጋር ሲወዳደር የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ ስለሚበልጥ ጉልህ ስታቲስትካዊ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም የመማር ማስተማር ሁኔታ የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮት መሆኑን ያመላክታል፡፡

አራተኛ የታየው ተግዳሮት ደግሞ ጭንቀት ሲሆን ተግዳሮቱን ለመወሰን የቀረበው ጥያቄ አራት ሲሆን እነሱም፡- በክፍል ውስጥ በተማሪዎች ፊት በአማርኛ መናገር ያስጨንቀኛል፣ በክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ለመሳተፍ እሳሳታለሁ ብዬ እፈራለሁ ፤ በክፍል ውስጥ ከመምህሩ እና ከክፍል ጓደኞቼ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ሳልጨነቅ ምላሽ እሰጣለሁ

እና በክፍል ውስጥ ውይይት የራሴን ሀሳብ ሳልፈራ እናገራለሁ ተብሎ ለቀረበው መጠይቅ ከተማሪዎች የተሰጠ ምላሽ በ"ቲ" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"ቲ" ዋጋ 8.57 ነው፡፡ በ161 የነፃነት ደረጃ የ"ቲ" ሰንጠረዥ ዋጋ 1.976 ነው፡፡ የተገኘው የ"ቲ" ቴስት ዋጋ 8.57 ከ"ቲ" ሰንጠረዥ ዋጋው 1.976 ጋር ሲወዳደር የተገኘው የ"ቲ" ቴስት ዋጋ ስለሚበልጥ የጎላ ስታቲስቲካዊ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም ጭንቀት የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት መሆኑን ያሳያል ፡፡

በአምስተኝነት የተገለፀው ደግሞ ስብዕና ሲሆን የተግዳሮት ደረጃን ለመለየት የቀረበው ጥያቄ ዘጠኝ ሲሆን እነሱም፡- በክፍል ውስጥ በንቃት እሳተፋለሁ፤ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም ያልተረዳሁትን ጥያቄ እጠይቃለሁ፤በክፍል ውስጥ በፈቃደኝነት ተሳትፎ አደርጋለሁ ፤በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በወይይት፣ በጥያቄና መልስ መሳተፍ ያስደስተኛል፤ ከመምህርና ከተማሪዎች ጋር በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተሳትፎ አደርጋለሁ ፤በክፍል ውስጥ የሚሰጠኝን ተግባር ለማከናወን ፈቃደኛ ነኝ ፤ የክፍል ጓደኞቼ ወይም መምህራን ስህተቴን ሲያርሙ ወይም ማስተካከያ ስሰጡ ለመቀበል ፈቃደኛ ነኝ ፤በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተሳትፎ ለማድረግ በራሴ እተማመናለሁ እና በክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ከመናገር ዝምታን እመርጣለሁ ተብሎ ለቀረበው መጠይቅ ላይ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በ"ቲ" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"ቲ" ዋጋ 3.8 ነው፡፡ በ161 የነፃነት ደረጃ፣ የ"ቲ" ሰንጠረዥ ዋጋ 1.976 ነው ፡፡ የተገኘው የ"ቲ" ቴስት ዋጋ 3.80 ከ"ቲ" ሰንጠረዥ ዋጋው 1.976 ጋር ሲወዳደር የተገኘው የ"ቲ" ቴስት ዋጋ ስለሚበልጥ የጎላ ስታቲስትካዊ ልዩነት አሳይቷል፡፡ በሌላ በኩል አማካይ ውጤቱ (Mean) በደረጃ ሲቀመጥ ስብዕና አምስተኛ ደረጃ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት መሆኑን ያሳያል፡፡

ስድስተኛ የተገለፀው አመለካከት ሲሆን የተግዳሮት ደረጃ ለመወሰን የቀረበው ጥያቄ ሦስት ሲሆን እነሱም፡-በክፍል ውስጥ በአማርኛ መናገር ያስደስተኛል ፤መምህሩ ጥያቄ ሲጠይቀኝ ለመመለስ ደስ ይለኛል እና በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ሌሎች ተማሪዎች ከእኔ የተሻሉ ናቸው ብዬ አስባለሁ ተብሎ በቀረበው መጠይቅ ላይ ከተማሪዎች የተሰጠው ምላሽ በ"ቲ"ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"ቲ" ዋጋ 2.81 ነው፡፡ በ161 የነፃነት ደረጃ፣ የ"ቲ" ሰንጠረዥ ዋጋ 1.976 ነው፡፡ የተገኘው የ"ቲ" ቴስት ዋጋ 2.81 ከ"ቲ" ሰንጠረዥ ዋጋው 1.976 ጋር

ሲወዳደር የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ ስለሚበልጥ የጎላ ስታቲስቲካዊ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም አመለካከት የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት መሆኑን ያሳያል፡፡

በሰባተኛ ደረጃ የተገለፀው ቋንቋ ሲሆን ተግዳሮትን ለመለየት የቀረበው ጥያቄ ሁለት ሲሆን እነሱም፡- በአማርኛ እንደ መጀመሪያ ቋንቋ መናገር እችላለሁ እና መምህሩ በአማርኛ ቋንቋ የሚናገረውን ነገር እረዳለሁ ተብሎ ለቀረበው መጠይቅ ከተማሪዎች የተሰጠ ምላሽ በ"t" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"t" ዋጋ -10.72 ነው፡፡ በ161 የነፃነት ደረጃ የ"t" ሰንጠረዥ ዋጋ 1.976 ነው፡፡ የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ -10.72 ከ"t" ሰንጠረዥ ዋጋው 1.976 ጋር ሲወዳደር የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ ስለሚበልጥ የጎላ ስታቲስቲካዊ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ከዚህም የምንረዳው ቋንቋ የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሚገድብ ተግዳሮት አንዱ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ስምንተኛ ደረጃ ተግዳሮት የትምህርት አቀራረብ ሲሆን ተግዳሮቱን ለመለየት የቀረበው ጥያቄ ሁለት ሲሆን እነሱም፡-መምህሩ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ በቡድን፣ በጥንድ እና በግል ያሳትፋሉ፣የአማርኛ መምህር የትምህርቱ አቀራረብ አሳታፊ ነው የሚል እና መምህሩ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ ጥያቄ አዘጋጅቶ ይጠይቃሉ ተብሎ ለቀረበው መጠይቅ ከተማሪዎች የተሰጠ ምላሽ በ"t" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"t" ዋጋ - -11.02 ነው፡፡ በ161 የነፃነት ደረጃ የ"t" ሰንጠረዥ ዋጋ 1.976 ነው፡፡ የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ -11.02 ከ"t" ሰንጠረዥ ዋጋው 1.976 ጋር ሲወዳደር ስለምበልጥ የጎላ ስታቲስቲካዊ ልዩነት አሳይቷል፡፡ከዚህም የምንረዳው ጠትምህርት አቀራረቡ የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሚገድብ ተግዳሮት አንዱ መሆኑን ያመላክታል፡፡

በዘጠነኛነት ከላይ ባለው ሠንጠረዥ በተገለፀው አማካይ ውጤት መሰረት የተገለፀው ፆታ ሲሆን ተግዳሮቱን ለመወሰን የቀረበው ጥያቄ አንድ ሲሆን እነሱም፡- በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ ተግባራት ወንዶችና ሴቶች በእኩል ተሳትፎ ያደርጋሉ ተብሎ ለቀረበው መጠይቅ ከተማሪዎች የተሰጠ ምላሽ በ"t" ቴስት ዋጋ ሲሰላ የተገኘው የ"t" ዋጋ -13.68 ነው፡፡ በ161 የነፃነት ደረጃ፣ የ"t" ሰንጠረዥ ዋጋ 1.976 ነው፡፡ የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ -13.68 ከ"t" ሰንጠረዥ ዋጋው 1.976 ጋር ሲወዳደር የተገኘው የ"t" ቴስት ዋጋ ስለሚበልጥ ጉልህ ስታቲስቲካዊ ልዩነት አሳይቷል፡፡ ይህም ፆታ የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት መሆኑን ያመላክታል፡፡

### 4.1.2 የክፍል ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶች በክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

በመማር ማስተማሩ ሂደት በተደረገው ምልከታ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመፈተሽ ከተማሪዎች አንፃር የተገኘው መረጃ አባሪ (ለ)ን ይመልከቱ፡

**ሰንጠረዥ 4.2 ከተማሪዎች አንፃር የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮት ለመፈተሽ የተካሄደ የክፍል ውስጥ ምልከታ መረጃ ትንተና**

| ተ.ቁ | ተማሪዎችን የተመለከቱ | አዎን | | አይደለም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ |
| 1 | ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎትና ተነሳሽነት አላቸው? | 2 | 16.6% | 10 | 83.4% |
| 2 | በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት ሁሉም ተማሪዎች ይሳተፋሉ? | 3 | 25% | 9 | 75% |
| 3 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያልተረዱትን ጥያቄ ይጠይቃሉ? | 5 | 41.6% | 7 | 58.4% |
| 4 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ? | 3 | 25% | 9 | 75% |
| 5 | በክፍል ውስጥ ለሚጠየቁት ጥያቄ ሳይፈሩ ምላሽ ይሰጣሉ? | - | - | 12 | 100% |
| 6 | በክፍል ውስጥ በፈቃደኝነት ተሳትፎ ያደርጋሉ? | 3 | 25% | 9 | 75% |
| 7 | በክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ሳይጨናነቁ ይናገራሉ? | 1 | 8.3% | 11 | 91.7% |
| 8 | በክፍል ውስጥ በቡድን ወይም በጥንድ በሚሰሩት ተግባር ላይ ከብጤዎቹ ጋር | 3 | 25% | 9 | 75% |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ሳይፈሩ ይወያያሉ? | | | | |
| 9 | ከመምህራቸው ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር ነፃ ሆነው በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ያደርጋሉ? | 1 | 8.3% | 11 | 91.7% |
| 10 | በአማርኛ ለመናገር ይፈልጋሉ? | - | - | 12 | 100% |
| 11 | በክፍል ውስጥ በቡድን፣ በጥንድና በግል ተሳትፎ ያደርጋሉ? | 4 | 33.3% | 8 | 66.7% |
| 12 | ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት ኃላፊነት ይወጣሉ? | 3 | 25% | 9 | 75% |
| 13 | ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት አስተያየት ይሰጣሉ? | 0 | - | 12 | 100% |
| 14 | በክፍል ውስጥ ወንዶችና ሴቶች በእኩል ደረጃ ይሳተፋሉ? | 3 | 25% | 9 | 75% |

ከሠንጠረዥ 4.2 ለማየት እንደሚቻለው (16.6%) ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች ተማሪዎች ለአማርኛ ትምህርት ያላቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑ ተስተውሏል፡፡ እንድሁም በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት አብዛኛው ተማሪዎች ሲሳተፉ አልታዩም ሆኖም በተወሰኑ (25%) ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች ተማሪዎች በቡድን ወይይት ሲሳተፉ ለማየት ተችሏል፡፡ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ መማር ማስተማር ሂደት ያልገባቸውን ወይም ያልተረዱትን ጥያቄ አልፎ አልፎ (41.6%) ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች ከመምህራቸው ወይም ከሌሎች ጓደኞቻቸው ጠይቀው ሲረዱ፤ በሌሎች (58.4%) ምልከታዎች ተማሪዎች ሲጠይቁ አልታዩም፡፡ በሌላ በኩል ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያላቸው ተሳትፎ (75%) ንቁ አይደሉም፤ ውስን ተማሪዎች ማለትም (25%) ብቻ ሲሳተፉ ታይቷል፡፡

በተመሳሳይ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የሚፈሩ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ሦስት ጊዜ (25%) በተደረገው ምልከታ

ተማሪዎች በፈቃደኝነት ተሳትፎ ሲያደርጉ አብዛኛው (75%) ምልከታ በተደረገበት ወቅት በራሳቸው ፈቃድ ሲሳተፉ አልተስተዋለም፡፡

ከዚህም ሌላ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በአማርኛ ለመናገር የሚጨነቁ፣ እንዲሁም በክፍል ውስጥ በቡድን ወይም በጥንድ በሚሰሩት ተግባር ከጓደኞቻቸው ጋር ለመወያየት፣ ለመነጋገርና ሀሳብ ለመስጠት በአብዛኛው (75%) ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች የሚፈሩ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡ ከመምህራቸው ጋርም ነፃ ሆነው ተሳትፎ የምያደርጉ (8.3%) ሲሆን (91.7%) በክፍል ውስጥ በአማርኛ ለመናገር የማይፈልጉ መሆናቸው ታይቷል፡፡

በሌላ በኩል (33.3%) ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች በቡድን፣ በጥንድና በግል ተሳትፎ የሚያደርጉ ሲሆኑ፤ (66.7%) ምልከታ በተደረገባቸው ክፍል ውስጥ ይህንኑ ሲተገብሩ አልታዩም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ምልከታ ከተደረገባቸው ክፍሎች (25%) ክፍል ውስጥ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ተግባራትን ሲያከናውኑና ኃላፊነት ለመወጣት ጥረት ሲያደርጉ፤ አብዛኛው (75%) ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች ውስጥ ተማሪዎች የቤት ስራ፣ የክፍል ስራ ሳይሰሩ በክፍል ውስጥ ታይተዋል፤ በተመሳሳይ ተማሪዎች ኃላፊነት ለመቀበል ያላቸው ጥረት አነስተኛና በመማር ማስተማር ሂደት ማንኛውንም አስተያየት የማይሰጡ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

በመጨረሻም (25%) በ (75%) ምልከታ በተካሄደባቸው ክፍሎች በክፍል ውስጥ ወንድና ሴት ተማሪዎች ያላቸው ተሳትፎ የሚመጣጠን ሆኖ አልታዬም፡፡

በተመሳሳይ በመማር ማስተማር ሂደት በተደረገው ምልከታ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ውሰጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመፈተሽ ከመምህራን አንፃር የተገኘው መረጃ በሰንጠረዥ 4.3 አባሪ (ሐ) ተመልክቷል፡፡

ሰንጠረዥ 4.3፡- ከመምህራን አንፃር የተማሪ ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመፈተሽ

የተደረገ የክፍል ምልከታ መረጃ

| ተ.ቁ | መምህራንን የተመለከቱ | አዎን | | አይደለም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ |
| 15 | መምህሩ ተማሪዎች ምን መስራት እንዳለባቸው ግልፅና ቀላል መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ይሰጣል? | 4 | 33.3% | 8 | 66.7% |
| 16 | መምህሩ ለተማሪዎች ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ይሰጣል? | 5 | 41.6% | 7 | 58.4% |
| 17 | መምህሩ ከተማሪዎች ጋር መልካም ግንኙነት አለው? | 4 | 33.3% | 8 | 66.7% |
| 18 | ተማሪዎችን በስም እየጠራ መምህሩ ያሳትፋል? | 2 | 16.6% | 10 | 83.4% |
| 19 | መምህሩ ሁሉን ተማሪ በእኩል ያሳትፋል? | 1 | 8.3% | 11 | 91.7% |
| 20 | የመምህሩ ባህሪ ለመማር ማስተማር ምቹ ነው? | 3 | 25% | 9 | 75% |
| 21 | መምህሩ የተማሪዎችን ተሳትፎ ያበረታታል? | 2 | 16.6% | 10 | 83.4% |
| 22 | መምህሩ እንደ ትምህርቱ አቀራረብ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴ እያለዋወጠ ይጠቀማል? | 2 | 16.6% | 10 | 83.4% |

ሰንጠረዥ 4.3 እንደተመለከተው መምህራን 4 ጊዜ 33.3% ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች ለተማሪዎች ምን መስራት እንዳለባቸው መመሪያ የሚሰጡ ቢሆንም የሚሰጡት መመሪያ ግልፅ ባለመሆኑ ተማሪዎች ሲቸገሩ ለማየት ተችሏል፡፡ እንዲሁም መምህሩ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ለሚጠይቁት ጥያቄ 8 ጊዜ 66.7% ምልከታ በተደረገባቸው

ክፍሎች ተገቢ ምላሽ ሲሰጡ አልታዩም፡፡ በተጨማሪ መምህሩ ከተማሪዎች ጋር ያለው ግንኙነት አነስተኛ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

ከዚህ ሌላ የተወሰኑ 2 ጊዜ 16.6% ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች መምህራን ተማሪዎችን በስም ጠርተው ሲያሳትፉ በርካታ 10 ጊዜ 83.4% ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች መምህራን ተማሪዎችን በስም ጠርተው የማያሳትፉ እንዲሁም የተማሪዎችን ተሳትፎ የማያበረታቱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመምህሩ ባህሪይ ለመማር ማስተማር በአብዛኛው 10 ጊዜ 83.4% ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች ምቹ አለመሆኑን እና መምህሩ እንደ ትምህርቱ ይዘት የማስተማሪያ ዘዴ እያለዋወጡ የማይጠቀሙ፤ ብዙውን ጊዜ 10 ጊዜ 83.4% በተደረገው ምልከታ ትምህርቱ መምህር መራሽ ገለፃ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

ቀጥሎ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመፈተሽ ከመማር ማስተማር ሁኔታዎች አንፃር የተገኘው መረጃ በሰንጠረዥ 4.4 ተመልክቷል ፡፡

ሰንጠረዥ 4.4፡- የመማር ማስተማር ሁኔታዎች በተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ ያለውን ተግዳሮት ለመፈተሽ የተደረገ ክፍል ምልከታ መረጃ ትንተና

| ተ.ቁ | የመማር ማስተማር ሁኔታን የተመለከቱ | አዎን | | አይደለም | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ድግግሞሽ | በመቶኛ | ድግግሞሽ | በመቶኛ |
| 23 | የክፍል ውስጥ የተማሪ አቀማመጥ ለተሳትፎ ምቹ ነው? | 5 | 41.6% | 7 | 58.3% |
| 24 | የተማሪዎች ቁጥር ለተሳትፎ ምቹ ነው? | - | | 12 | 100% |
| 25 | የመማሪያ ክፍል ውስጥ ለመማር ማስተማር ምቹ ነው? | 4 | 33.3% | 8 | 66.7% |

ከሠንጠረዥ 4.4 ማየት እንደሚቻለው 7 ጊዜ 58.3% ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች የተማሪዎች አቀማመጥ ተሳትፎ ለማድረግ አመቺ አይደለም፡፡ የተማሪዎች ክፍል ውስጥ አቀማመጥም ረድፍዊ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ እንዲሁም የተማሪ ቁጥር 12 ጊዜ 100% ምልከታ በተደረገባቸው ክፍሎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ምቹ አልነበረም፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥም ከማረሚያ ትምህርት ቤት ውጭ ከ60 እስከ 70 ተማሪዎች መኖራቸው ፣ በሌላ በኩል በመማሪያ ክፍል በቂ የሆነ ጠረጴዛና ወንበር አልነበረም፣ የክፍል ውስጥ ስፋት ከተማሪ ቁጥር ጋር የማይመጣጠንና ክፍሉ ያረጀ በመሆኑ ለመማር ማስተማር ያለው ምቹት አነስተኛ መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡

### 4.1.3 ፡- በቃለ መጠይቅ ከተማሪዎች እና ከመምህራን የተገኘው መረጃ ትንተና

## 4.1.3.1 ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ ትንተና

በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ተሳትፎ እንዳያደርጉ ተግዳሮት የሚሆኑ መሰናክሎች ምንድናቸው የሚል በመጀመሪያ ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄ ሲሆን "ዋንኛው መሰናክል አማርኛን ከሦስተኛ ክፍል ጀምሮ እንደ አንድ ትምህርት ስለምንማር ቋንቋን ያለመቻል መሆኑን ገልፀዋል"፡፡ ቋንቋ ሀሳባችንን የሚንገልፅበት፣ጥያቄ የሚንጠይቅበት እና ምላሽ የምንሰጥበት ዋነኛ መሳሪያ ቢሆንም ተማሪዎች ይስቁብናል በመምህራን ፊትም ያስፈራ ይሆናል በሚል ሥጋትና ፍርሃት ተሳትፎ ለማድረግ እንቸገራለን ሲሉ ከተጠየቁት ዘጠኝ ተማሪዎች መካከል ሰባት ተማሪዎች ገልፀዋሉ፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት የሚሆኑ ነገሮች ለቋንቋ ትምህርት ዕድገት ተግዳሮት ይሆናል ብለው ያስባሉ ለተባለው "ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለትምህርቱ ያላቸው አመለካከት፣ተነሳሽነት ማነስ፣የራሳቸውን ምላሽ ትክክል ይሆናል ብለው አለማሰብ፣ በትምህርቱ ተግባር ደስተኛ ያለመሆን፣ትምህርቱን በሙሉ ስሜት ያለመከታተል በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ተግባራት ለማከናወን ፈቃደኛ ያለመሆን፣ በራስ መተማመን ያለመኖር፣ ለትምህርቱ የሚሰጡት ግምት ወይም ቦታ አነስተኛ መሆን ለቋንቋ ዕድገትም ሆነ ለክፍል ተሳትፎ ትልቅ ተግዳሮት ነው በማለት ተናግረዋሉ"፡፡

በመቀጠልም በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ለመናገር ትፈራላችሁ? ምክንያቱ ምንድነው ? ተብለው ለተጠየቁት "ተማሪዎች ከሚገባ በላይ እንደሚፈሩና ለዚህም ቁልፍ ችግሩ በቋንቋ ላይ በቂ ዕውቀት የሌላቸው መሆኑን ተናግረዋሉ" ፡፡

በተጨማሪ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተማሪ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መምህራቹ ይጠቀማል ? የሚጠቀሙ ከሆነ በምን ዓይነት መንገድ እንድትሳተፉ ያደርጋል ? ለተባሉት "መምህሩ በክፍል ውስጥ አልፎ አልፎ የቤት ሥራና የክፍል ሥራ አብሮ ከሚሰሩት በስተቀር በአብዛኛው የሚጠቀሙት በመምህር የሚመራ ገለፃ ዘዴ መሆኑን ገልፀዋል"፡፡

ሌላው በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ከወንድና ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ የትኞቹ ናቸው? ለምን? ከዘጠኝ መላሾች ስምንቱ (አብዛኛው መላሾች) በክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉት "ወንዶች መሆናቸውን ገልፀዋል" "ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሌሎች ተማሪዎችን በመፍራት በራስ መተማመን እንደሚያጡና ተሳትፎ እንደማያደርጉ ጠቁመዋል"፡፡

በሌላ በኩል በአማርኛ ቋንቋ ለመናገር ያላችሁ አመለካከት ምን ይመስላል? ለሚለው ጥያቄ "ተማሪዎች በአማርኛ ለመናገር ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ መሆኑን ገልፀዋል"፡፡ በመቀጠል መምህራችሁ በክፍል ውስጥ ተግባራት በእኩል ያሳትፋሉ? ተብለው ለተጠየቁት መምህራን "በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በእኩል አያሳትፉም"፣ የሚያሳትፉት "ጎበዝ የሆኑትን፣ ፈጥነው እጅ የሚያወጡትንና በስም የሚያውቋቸውን ተማሪዎች ብቻ መሆኑን" ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በመጨረሻም መምህራችሁ በተለያዩ ተግባራት ተሳትፎ ስታደርጉ ያበረታታሉ? ለተሳትፏችሁ አዎንታዊ ምላሽ ይሰጣሉ? ለሚለው ጥያቄ "በክፍል ውስጥ መምህራን የሚሰጡት ማበረታቻ ዝቅተኛ እና የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽ አዎንታዊ ሳይሆን ተማሪዎችን የሚያሸማቅቁ፣ የሚቆጡ፣የሚያስፈራሩ፣አምባገነንና አልፎ አልፎም ጥሩ ስሜት የሌላቸው መሆኑን ገልፀዋል"፡፡ በተመሳሳይ በቃለ መጠይቅ አማካኝነት በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመለየት ከመምህራን የተገኘው መረጃ ትንተና ፡፡

## 4.1.3.2 ፡- ከመምህራን የተገኘው መረጃ ትንተና (አባሪ ሠ)

በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት የሚሆኑ መሰናክሎች ምንድን ናቸው? ተብለው ለተጠየቁት መምህራን በተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት ከሚሆኑ ዋንኛውና መሰረታዊ የሆነው "የቋንቋ ችግር እንደሆነ ይገልፃሉ"፡፡ ቋንቋ ለተማሪዎች የአፍ መፍቻ ባለመሆኑ ተማሪዎች ቋንቋውን የሚያገኙት በክፍል ውስጥ ብቻ ነው፡፡ ተማሪዎች ከማህበረሰቡ ጋር መስተጋብር የሚፈጥሩት በአፍ መፍቻ ቋንቋ ነው ፡፡ ለቋንቋ ተጋልጦ የሌላቸው መሆኑ አንዱ ተሳትፎ እንዳያደርጉ የሚገድብ ተግዳሮት እንደሚሆን ገልፀዋል፡፡

ሌላው ተማሪዎች "ቋንቋ ለመማር ያላቸው አመለካከትና ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆን፣ ስህተት ይፈጠራል የማለት ስጋት፣ ፍርሃት፣ ከጓደኞቻቸው የሚደርስባቸው ሳቅ፣ የጭንቀት ስሜት ውስጥ መግባት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ከፍተኛ ተግዳሮት መሆኑን ገልፀዋል"፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያላቸው ስብዕና በክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት በመሆን ትልቁን ስፍራ የሚይዝ ነው ሲሉ ገልፀዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በክፍል ውስጥ ጥቂት ተማሪዎች ጥያቄ ለመመለስ፣ ለመጠየቅና አስተያየት ለመስጠት ፍላጎት ሲኖራቸው አብዛኛው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ አስተያየት የማይሰጡ፣ ጥያቄ የማይጠይቁና የማይመልሱ እንዲሁም የቤትና የክፍል ስራ የማይሰሩ፣ በቡድን በጥንድ ለመሳተፍ የማይፈልጉ ዝም ብለው የሚቀመጡ ተመልካች ናቸው፡፡ በተመሳሳይ ተማሪዎች ቋንቋውን አልችለውም በማለት የሚሰጡት ግምት ወይም ለራሳቸው የሚሰጡት ስፍራ ዝቅተኛ መሆን፣ በራስ መተማመን ማጣት በክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት የሚሆኑ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ሌላው በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች ተሳትፎ ለማድረግ ይፈራሉ ብለው ያስባሉ? ምክንያቱ ምንድነው? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን አዎን የሚል ምላሽ

ሰጥተዋል፡፡ ምክንያቱንም ሲገልጹ ተማሪዎች በቋንቋው የዕውቀት ውስንነት ስላላቸው ስህተት እፈፅማለው ብለው ስለሚሰጉ ይፈራሉ የሚል አስተያየት ሰተዋል ፡፡

በመቀጠል ተማሪ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ ይጠቀማሉ? የሚጠቀሙ ከሆነ በምን አይነት ዘዴ እንዲሳተፉ ያደርጋሉ? ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን ተማሪ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ የማይጠቀሙ፤ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ በቡድን፣ በጥንድና በግል የቤት ስራ የክፍል ስራ እንዲሰሩ በማድረግ የማያሳትፉና በአብዛኛው ትምህርቱን በገለፃ የሚያቀርቡ መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡

ከዚህም ሌላ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ከወንድና ሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉ የትኞቹ ናቸው? ለምን? ለሚለው ጥያቄ ወንድ ተማሪዎች መሆናቸውን ገልፀው ምክንያቱም ወንዶች በክፍል ውስጥ ለመናገር ያላቸው ድፍረት ከሴት ተማሪዎች የተሻለ ነው ሴቶች ግን በአብዛኛው በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ድፍረትና በራስ መተማመን ይጎላቸዋል በማለት ተናግረዋል፡፡

ሌላው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል? ተብለው ለተጠየቁት መምህራን ተማሪዎች ለቋንቋው ያላቸው እይታ ዝቅተኛ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ በእኩል ያሳትፋሉ? ለተባሉት ሁሉም መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በእኩል የማያሳትፉ፣ በአብዛኛው ጎበዝ የሆኑትንና ቀድመው እጅ የሚያወጡትን ብቻ እንደሚያሳትፉ ገልፀዋል፡፡ በመጨረሻም ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት ተሳትፎ ሲያደርጉ ያበረታታሉ? ለተማሪዎች ተሳትፎ አዎንታዊ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ? ተብለው ለተጠየቁት መምህራን በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሲያደርጉ ሁል ጊዜ ባይሆንም አልፎ አልፎ እንደሚያበረታቱና አዎንታዊ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡ መሆኑን ገልፀው፣ ነገር ግን በቂ እንዳልሆነ ተናግረዋል፡፡

የጥናቱ ሁለተኛው መሰረታዊ ጥያቄ የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶች በቋንቋ ትምህርት የሚኖራቸው አንድምታ ምንድን ነው? የሚል ሲሆን ይህን ለመመርመር በክፍት መጠይቅና በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ትንተና እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡
ለተማሪዎች በቀረበው ክፍት መጠይቅ እንደተገለፀው በክፍል ተሳትፏቸው ላይ ተግዳሮት የሚሆኑ በአማርኛ ትምህርት ላይም ተግዳሮት አለው፡፡ ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲጠሉ፣

በትምህርቱ ከሌሎች ትምህርት ይልቅ ዝቅተኛ ውጤት እንዲያስመዘግቡ፣ እርስ በርስ በአማርኛ እንዳይነጋገሩ፣ ነፃ ሆነው ሀሳብ እንዳይገልፁ እና በክፍል ውስጥ በቋንቋ ተጠቅመው እንዳይጠይቁ፣ እንዳይመልሱ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወት በትምህርቱ ላይ አሉታዊ አስተዋፆኦ አለው በማለት ገልፀዋል፡፡

በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ተማሪዎች ትምህርቱን እንዲፈሩ፣ ቋንቋውን እንዲጠሉ፣ በትምህርቱ ውጤታማ እንዳይሆኑ፣ በቋንቋው እርስ በርስ እንዳይነጋገሩና ከትምህርቱ ማግኘት የሚገባውን ክሂልና ዕውቀት በተገቢ ሁኔታ እንዳያገኙ በማድረግ አሉታዊ ተግዳሮት የሚፈጥር መሆኑን ገልፀዋል፡፡

በተመሳሳይ ለመምህራን በቀረበው ቃለ መጠይቅ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች በተማሪዎች ቋንቋ ክሂሎት ላይ ተግዳሮት አለው ብለው ያስባሉ? አለ ካሉ ምን አይነት ተግዳሮት አለው? ይግለፁ፡፡ ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ መምህራን ተግዳሮት አለው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ተግዳሮቱም በተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎት ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ሊሆኑ የሚችሉ ቢሆንም ከትምህርት ቤቱ አንፃር ተማሪዎች በአማርኛ እርስ በርስ እንዳይነጋገሩ፤ ከመምህራንና ከጓደኞቻቸው ጋር መስተጋብር እንዳይፈጥሩ፤ ሀሳብ እንዳይሰጡ፣ በክፍል ውስጥ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ምላሽ እንዳይሰጡ፣እርስ በርስ የተግባቦት ችሎታ እንዳያሳድጉና ቋንቋውን እንዳይጠቀሙ የሚያደርግ በመሆኑ በተማሪዎች ቋንቋ ክሂሎት ላይ አሉታዊ ተግዳሮት የሚያደርስ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

## 4.2 የውጤት ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ትኩረት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መፈለግ ነው፡፡ በመሆኑም በጽሑፍ መጠይቅ፣ በክፍል ምልከታና በቃለ መጠይቅ በተሰበሰቡት መረጃዎች የተማሪዎች ክፍል ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመፈተሽና በተማሪዎች ቋንቋ ክሂሎት ላይ የሚደርሱት ተግዳሮት ለመመርመር መረጃዎች በገላጭ ስታቲስቲክሶች ተተንትነዋል፡፡

### 4.2.1 በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መፈተሽ

በውጤት ትንተናው በቅድሚያ ምላሽ የተሰጠው በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮት አለ የሚለውን የሚመለከት ነው፡፡ በፅሁፍ መጠይቅ ትንተና ውጤት መሰረት በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች በስታትስቲክስ ጉልህነት ($p<0.05$) ሆኖ በመገኘቱ የክፍል ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት መኖሩን አመላክቷል፡፡ በሌላ በኩል በአማካይ ውጤት ደረጃ መሰረትም የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮት መኖራቸውን አሳይቷል፡፡

በተመሳሳይ ከተማሪዎች ፅሁፍ መጠይቅ፣ ከክፍል ምልከታ እና ከተማሪዎችና መምህራን ቃለ መጠይቅ የተገኙ መረጃ ትንተና ውጤት የመምህሩ ባህሪ፣የመማር ማስተማር ሁኔታዎች፣ ተነሳሽነት፣ የመምህሩ ትምህርት አቀራረብ፣ ስብዕና፣ አመለካከት፣ ያታ፣ጭንቀት፣የተማሪዎች ቋንቋ ደረጃ፣የትምህርት አቀራረብ፣ተማሪዎች በራስ መተማመን ማጣት፣ፍረሃት፣በክፍል ውስጥ ኃላፍነት አለመቀበል፣ ፍላጎት አለመኖርና ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ መሆናቸውን አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ የፅሑፍ መጠይቅ፣ የክፍል ምልከታና የቃለ መጠይቅ መረጃ ትንተና ውጤት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት መኖሩን አሳይቷል፡፡ ይህም Peteris (2000)፣ Liu (2005)፣ Green.D.(2008)፣ Liu& Jackson (2008)ና Liu&Li (2011) ጥናት ውጤት ጋር የተስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በጥናቱ ውጤት መሰረት መምህራን ትምህርቱን የሚያቀርቡበት የማስተማሪያ ዘዴ ተማሪ አሳታፊ ያለመሆን፤ መምህራን በክፍል ውስጥ ያላቸው ባህሪ ምቹ ያለመሆን፣ መምህራን ተማሪዎችን በአባታዊነት እና በእናታዊነት ስሜት የሚደግፉ ሳይሆኑ ቀርተው የሚያሸማቅቁ፣ አምባገነን ሆነው ሲገኙ፤ በሌላ በኩል ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው ተነሳሽነትና አመለካከት አዎንታዊ አለመሆን፤ በክፍል ውስጥ ቋንቋ ትምህርት ሲማሩ ያላቸው ጭንቀት፣ ፍርሃት፤ በሌላ በኩል የተማሪዎች ያታ ልዩነትና የመማር ማስተማር ሁኔታዎች ምቹ አለመሆን በተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት ሆነዋል ፡፡ የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመለየት

በቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተገኘው መረጃ በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቷል፡፡

በሰንጠረዥ 4.2 እንደ ተመለከተው በተማሪዎች መጠይቅ ውጤት ትንተና መሠረት በአንደኛ ደረጃ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የተማሪዎች ክፍል ተሳትፎን የሚገድበው ተግዳሮት የመምህሩ ባህሪ ነዉ፡፡ የመምህሩ ባህሪ በክፍል ወስጥ ያለዉን ተግዳሮት ለማወቅ ለቀረበዉ ጥያቄ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘዉ ምላሽ መምህራን ሲያስተምሩ ያላቸው ባህሪ ምቹ ባለመሆኑ ተሳትፎ ለማድረግ አዳጋች ነው፡፡ በተጨማሪም በክፍት መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው መምህራን በክፍል ውስጥ የማንቋሸሽ፣ የመቆጣት፣ የማስፈራራት ባህሪ ስለሚታይባቸው ተማሪዎች ተሳትፎ ለማድረግ የሚፈሩ መሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል፡፡

በተመሳሳይ በመማር ማስተማር ሂደት ከተደረገው ምልከታ ለመረዳት እንደተቻለው መምህራን ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዲያደረጉ የሚያበረታቱ ሳይሆን የሚያሸማቅቁ፣ ቁጡ እና አምባገነን መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

በተጨማሪም ከተማሪዎች ቃለ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ መምህራን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሲያደርጉ የማያበረታቱ፣ አዎንታዊ ምጋቤ ምላሽ የማይሰጡ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ ከመምህራን በቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃም ይህንን የሚያጎላ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

መምህራን በክፍል ውስጥ ተማሪዎችን በአባታዊ ስሜት የሚያዩ፣ በመልካም መንፈስ እንደ ጓደኛ የሚያቀርቡ፣ የሚያበረታቱና የሚደግፉ ከሆነ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት ይጨምራል፡፡ በአንፃሩ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚሳደቡ፣ የሚያንቋሽሹ፣ ተማሪዎችን የሚያስፈራሩና ቁጡ ከሆኑ በተማሪዎች መማር አልፎም በክፍል ተሳትፎ ላይ አዳጋች ነገር ይፈጥራል፡፡ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው ፍላጎትም ዝቅተኛ ይሆናል፡፡

በአጠቃላይ በፅሁፍ መጠይቅ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃም ሆነ ከክፍል ምልከታና ቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ውጤት የመምህራን ባህሪ በተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ ላይ

ተግዳሮት እንዳለው ጠቁሟል፡፡ ይህን አስመልክቶ Berdine(1986)፤ መምህራን ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ የማይቆጣጠሩ፣ቸልተኞች፣ተማሪዎችን በበታችነት ስሜት የሚያዩ፣ ተማሪዎችን የሚሳደቡ፣ የሚያንቋሽሹ እና የሚያስፈራሩ ከሆነ የተማሪዎች የመማር ሂደትን የሚያደናቅፍ እና የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚጎዳ ነው በማለት ከገለፁት ሀሳብ ጋር የተስማማ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ሁለተኛ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሚገድቡት ውስጥ አንዱ የመማር ማስተማር ሁኔታዎች ናቸው፡፡ የመማር ማስተማር ሁኔታዎች ምቹ መሆን ወይም ያለመሆን የክፍል ተሳትፎን ይወስናል፡፡ በመሆኑም ለተማሪዎች በቀረበው መጠይቅ ውጤት መሰረት የመማር ማስተማር ሁኔታዎች የተማሪ ክፍል ተሳትፎን የሚገድብ ተግዳሮት እንደሆነ ያመላክታል፡፡

በክፍል ውስጥ ምልከታ በተደረገበት ወቅት የተማሪ ቁጥር ከፍተኛ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ በአማካይ ከ60 እስከ 70 ተማሪዎች እንዳሉ ለመታዘብ ተችሏል፡፡ ይህም Rocca (2009) በአንድ ክፍል ውስጥ ከአርባ እስከ ሃምሳ ተማሪዎች ቢኖሩ ይመረጣል፤ ያሉትንና Yulies (1976) በአንድ ክፍል ውስጥ ከሃያ እስከ አርባ ቢሆን የተሻለ ነው ያሉትን ሀሳብ የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በተመሳሳይ Weaver እና Qi (2005) በበኩላቸው የተማሪ ቁጥር እንደየተቋሙ የሚወሰን ቢሆንም በአንድ ክፍል ውስጥ ከሰላሳ እስከ አርባ ተማሪዎች ብቻ እንዲገኙ ይመክራል፡፡

በተጨማሪ Weaver እና Qi (2005) ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ተግዳሮት ከሚፈጥሩት ከመማር ማስተማር ሁኔታዎች አንዱ በአንድ ክፍል የተማሪ ቁጥር መብዛት ነው፡፡ ብዙ ተማሪዎች ባሉበት ክፍል ውስጥ ተማሪዎች ተሳትፎ ለማድረግ ይፈራሉ፤ በሌላ በኩል የተማሪዎች ቁጥር ሲያንስ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ያላቸው ፍላጎት ይጨምራል፡፡ መምህራን ተማሪዎችን ለይተው እንዲያውቁና ተገቢ የሆነ እገዛ እንዲያደርጉ ይረዳል፡፡ ተማሪዎችም ተሳትፎ የማድረግ ዕድላቸው ከፍተኛ ይሆናል ያሉትን ሀሳብ የሚቃረን ነው፡፡

የመማሪያ ክፍል ውስጥ አቀማመጥ በተማሪ ክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት ከሚሆኑት ከመማር ማስተማር ሁኔታዎች አንዱ ነው፡፡ በክፍል ውስጥ የተማሪዎች አቀማመጥ ምቹ

መሆን አለመሆን፣ የተለያዩ የአቀማመጥ ስልት መጠቀም አለመጠቀም በክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት አለው Rocca (2009)፡፡ በተመሳሳይ Fassinger (1995a) ጥንታዊ የሆነ መስመራዊ ወይም ረድፋዊ አቀማመጥ፣ ፈረስ ኮቴ ወይም ግማሽ ክብ አቀማመጥ ካላቸው ተማሪዎች ጋር ሲታዩ ዝቅተኛ ተሳትፎ እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ አንፃር በክፍል ውስጥ ምልከታ ወቅት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ቀጥተኛ ወይም ረድፋዊ አቀማመጥ ያላቸውና በክፍል ውስጥ ምቹ ጠረጴዛና መቀመጫ ወይም ወንበር ያልተሟላ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

ለጥናቱ በተመረጡት ትምህርት ቤቶች በተማሪዎች መጠይቅ እና በምልከታው የተገኘው መረጃ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የተማሪ አቀማመጥ ምቹ ባለመሆኑ በተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት እንዳለው አሳይቷል፡፡ ይህም Rocca (2009) እና Fassinger (1995a) የተማሪዎች አቀማመጥ በክፍል ውስጥ ምቹ መሆን ወይም አለመሆን በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተግዳሮት አለው፣ ያሉትን ሀሳብ የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በአጠቃላይ በምልከታ ከክፍል ውስጥ የተሰበሰበው መረጃ ውጤት የመማር ማስተማር ሁኔታዎች በተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት ያለው መሆኑን ያሳያል፡፡ ይህም Liu, M,H(2011) የመማር ማስተማር ሁኔታዎች ምቹ ያለመሆን የተማሪዎችን መማር ያላቸው ተሳትፎ በአሉታ መልክ ይወስናል፣ያሉትን ሀሳብ የሚጋራ ነው፡፡

ሌላው ተሳትፎን ከሚገድቡት ተግዳሮቶች ሶስተኛ ደረጃ የሚይዘው ተነሳሽነት ሲሆን፣ የተማሪዎች ተነሳሽነት በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ተግዳሮት ያለ መሆኑን ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ መረጃ ያመለክታል፡፡ በተመሳሳይ ከምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለቋንቋ ትምህርት ያላቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት ዝቅተኛ መሆኑን ነው፡፡ ይህ ደግሞ በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ተግዳሮት መሆኑን ያመለክታል፡፡

Williamsእና Berdine (1971) ተማሪዎች ለመድረስ ከሚፈልጉት ግብ አንፃር ውስጣዊና ውጫዊ ተነሳስቶ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ውስጣዊ ተነሳሽነት ከግለሰቡ ራሱ የሚመነጭ በመሆኑ በቋንቋ ለመዝናናት እና ቋንቋን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነት ሲሆን ውጫዊ

ተነሳሽነት ተማሪዎች ፈተና ለማለፍ እና ሽልማት ለማግኘት ሲሉ ያላቸው የመማር ተነሳሽነት ነው፡፡

Schumann (1975) ተነሳሽነት ከቋንቋ መማር ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ያለው በመሆኑ ተማሪዎች በትምህርት ተግባር ላይ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ወይም እንዳያደርጉ የማድረግ ኃይል አለው በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት በመማር ሂደት ተነሳሽነት ለቋንቋ ትምህርት ስኬት ያለው አስተዋጽኦ ጉልህ ሲሆን፣ ስኬት የሚታየው ደግሞ ከረጅም ጊዜ ጥረት በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ በቋንቋ መማር ስኬታማ ለመሆን ወይም ያላቸውን የቋንቋ ክሂል ለማሻሻል ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተግባራት በተነሳሽነት ሊሳተፉ ይገባል፡፡

በተመሳሳይ Farrant; (1980) ተነሳሽነት ተማሪዎች ትምህርቱን ሲማሩ ካላቸው ግብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው ይሉና ተማሪዎች ግባቸው ውስን ከሆነ ተነሳሽነታቸው የተዳከመ ይሆናል በማለት ያስረዳሉ፡፡

በአጠቃላይ ከውጤት ትንተናው መረዳት እንደሚቻለውም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች ተነሳሽነት የሌላቸው በመሆኑ በክፍል ውስጥ ተሳትፏቸው ላይ ተግዳሮት ማሳየቱ Farrant; ና ሌሎች የዘርፉ ምሁራን ከገለጹት ሀሳብ ጋር ጥናቱ የሚያሳየው ውጤት የሚዛመድ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ተነሳሽነት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ እንዳያደርጉ ከፍተኛ ተግዳሮት በመሆን በሶስተኛ ደረጃ ተሳትፎን የሚገድብ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡

የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሚገድቡ ተግዳሮቶች አንዱ ጭንቀት ነው፡፡ ይህን ለመለየት ለተማሪዎች ከቀረበው መጠይቅ ከተገኘው መረጃ ትንተና ውጤት ጭንቀት አራተኛ ደረጃ የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት መሆኑን አመላክቷል፡፡

በተመሳሳይ በምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ የሚፈሩ እና የራሳቸውን ሀሳብ ከመስጠት የሚቆጠቡ መሆናቸው ተስተውሏል፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በጓደኞቻቸው ፊት ለመናገር ወይም ተሳትፎ

ለማድረግ ስህተት ይፈጠራል ብለው የሚፈሩ፣ የራሳቸውን ሀሳብ ለመግለፅ ስጋት ውስጥ የሚገቡ መሆናቸውን ተስተውሏል፡፡

ለተማሪዎች ከቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ እና በክፍል ውስጥ ከተከናወነው ምልከታ እንዲሁም ከቃለ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤቶች የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ያላቸው ጭንቀት የክፍል ተሳትፎን የሚገድብ ተግዳሮት መሆኑን ያሳያል፡፡

ይህም Cohen(1986) ጭንቀት በሰዎች ሰሜት ላይ ተግዳሮት በመሆን በቋንቋ ትምህርት ያላቸውን ቁርጠኝነት የሚያሳጣ መሆኑን ከገለፁትና Brown(2000) ጭንቀት በተማሪዎች ላይ ውጥረት፣ ፍርሃትና የንዴት ስሜት ተዳምረው የሚፈጥሩት የነርቭ ስርዓት በመሆኑ የመማር ሂደትን ሊያውክ የሚችል ነው ካሉት ጋር የሚዛመድ ነው፡፡ በመሆኑም ጭንቀት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ በመወሰን አራተኛ ደረጃ ተግዳሮት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

አጥኝዋ ለተማሪዎች ካቀረበችው መጠይቅ ያገኘችው መረጃ ውጤት ትንተና እንደሚያሳየው የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሚገድቡት ውስጥ ስብዕና አምስተኛ ደረጃ ተግዳሮት እንዳለው አመላክቷል፡፡ በተመሳሳይ በክፍት መጠይቅ የተገኘው መረጃ ውጤት ትንተና ይህንኑ የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በመማር ማስተማር ሂደት በተካሄደው የክፍል ምልከታ ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት ሀሳብ ከመሰጠት ይልቅ ዝምታን የሚመርጡ፤ተሳትፎ ለማድረግ ፈቃደኝነት የሌላቸው፤ በክፍል ውስጥ ውይይት ለማድረግ፣ ለመጠየቅና ለመመለስ ደስተኛ ያለመሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡

በጽሑፍ መጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች የተሰበሰበውም ሆነ በምልከታ የተገኘው መረጃ ውጤት ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች ስብዕና የክፍል ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት መሆኑን አሳይቷል፡፡ ይህም Lee (2005)፤ Brown (2000) አብዛኛው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳታፊዎች አይደሉም፤ በክፍል ውስጥ ለመወያየት፣ ጥያቄ ለመጠየቅ፣ አስተያየት ለመስጠት አይፈልጉም፡፡ የዚህ አይነት ተማሪዎች ጭምትነት ባህሪ ያላቸው በመሆኑ በክፍል ውስጥ ፍዝ ተሳታፊዎች ናቸው፤ ያሉትን ሀሳብ የሚያጠናክር

ነው፡፡ በመሆኑም ስብዕና በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድብ አምስተኛ ደረጃ ተግዳሮት እንደሆነ የዚህ ጥናት ውጤት ያስረዳል፡፡

በመቀጠል የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎን የሚገድብ ተግዳሮት የተማሪዎች አመለካከት ነው፡፡ አመለካከትን በተመለከተ ለተማሪዎች ከቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ውጤት በስድስተኛ ደረጃ ተግዳሮት እንዳለው አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም ከተማሪዎችና ከመምህራን ቃለ መጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ ውጤት ተማሪዎች ለቋንቋው ያላቸው አመለካከት አሉታዊ መሆኑን ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ ከተማሪዎች በጽሑፍና በቃለ መጠይቅ ተሰብስበው በተገኘው መረጃ ትንተና ውጤት መሰረት አመለካከት የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮ መሆኑን አሳይቷል፡፡ ይህም Green (2008) በክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት ከሆኑት አንዱ ተማሪዎች ለትምህርቱ ያላቸው አሉታዊ አመለካከት ነው ያሉትን ሀሳብና Schumann (1975) ተማሪዎች በቋንቋ ላይ የሚኖራቸው አመለካከት በቋንቋ መማር ሂደት ለትምህር የሚኖራቸውን እይታ ይወስናል ያሉትን ሀሳብ የሚጋራ ነው፡፡ በመሆኑም በቋንቋ መማር ሂደት ተማሪዎች ለቋንቋ አዎንታዊ አመለካከት ቢኖራቸው የተሻለ ነው፡፡ ተማሪዎች አዎንታዊ አመለካከት ሲኖራቸው በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ በሌላ በኩል አመለካከታቸው አሉታዊ ሲሆን ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ይሆናል፡፡ በመሆኑም በጥናቱ ውጤት መሰረት አመለካከት ስድስተኛው ተግዳሮት አድራሽ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመለየት በቀረበው የፅሁፍ መጠይቅ አማካኝነት የተገኘው መረጃ በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ የተገኘው ውጤት ያሳያል፡፡ በሰንጠረዥ 4.1 እንደተመለከተው በተማሪዎች መጠይቅ ውጤት ትንተና መሰረት በተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት ከሚሆኑት መሰናክሎች አንዱ የተማሪዎች የቋንቋ ደረጃ ነው፡፡ በጽሑፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ ውጤት መሰረት ተማሪዎች በአማርኛ ለመናገር የሚቸገሩና መምህራን በአማርኛ የሚናገሩትን ነገር ለመረዳት የሚያዳግታቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተመሳሳይ በክፍት መጠይቅ ከተገኘው መረጃ በክፍል ውስጥ በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት ከሚሆኑት አንዱ የቋንቋ ደረጃ እንደሆነ ከገለፁት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

በክፍል ውስጥ ምልከታ በተደረገበት ወቅት ተማሪዎች የሚሰጣቸውን ተግባራት ለማከናወን በአማርኛ ቋንቋ እንደማይጠቀሙና በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የተሰጣቸውን ተግባር ለማከናወን ሲነጋገሩ ለማዳመጥ ተችሏል፡፡ ይህም የተማሪዎች የቋንቋ ደረጃ ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በተጨማሪም ከተማሪዎችና ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚጠቁመው በክፍል ውስጥ ተሳትፎን ከሚገድቡ ተግዳሮቶች የተማሪዎች የቋንቋ ደረጃ አንዱ መሆኑን ሲገልፁ ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን የሚያገኙት በክፍል ውስጥ ብቻ በመሆኑ ከክፍል ውጭ ተጋልጦ የላቸውም፡፡ በመሆኑም በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ እሳሰታለሁ በማለት በፍረሃት እና ጭንቀት ስሜት ውስጥ በመግባት ተሳትፎ እንደማያደርጉ ከሰጡት ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

ከተማሪዎችና ከመምህራን የተገኘው መረጃ ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤቶች የተማሪዎች የቋንቋ ደረጃ በተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ ላይ ከፍተኛ ተግዳሮት ያለው መሆኑን ያመላክታል፡፡ ይህም Brown (2000) Li, & Liu 2011) ፤ ተማሪዎች በቋንቋው ያላቸው ደረጃ ዝቅተኛ ከሆነ ስህተት እፈፅማለሁ ብለው ስለሚፈሩ ተሳትፎ ለማድረግ አይፈልጉም ያሉትን ሀሳብ የሚደግፍ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡ ይህም ለተማሪዎች በቀረበዉ መጠይቅ ሰባተኛ ደረጃ ተሳትፎ የሚገድብ ተግዳሮት ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

በስምንተኛ ደረጃ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎች ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሚገድቡት ውስጥ የትምህርት አቀራረብ ነው፡፡ በመማር ማስተማር ሂደት በክፍል ምልከታ ወቅትም የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ በቡድን፣ በጥንድ እና በግል የክፍል ውስጥ ተግባራትን ሲያሰሩ አልታዩም፡፡ በተጨማሪ መምህራን ተማሪዎችን በተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን ተጠቅመው ንቁ ተሳትፍ ለማድረግ ሲጥሩ አልተስተዋለም፡፡ ከተማሪዎችና ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃም ከክፍል ምልከታው ጋር ተመሳሳይነት ባለው መልኩ መምህራን በአብዛኛው የሚጠቀሙት በመምህር የሚመራ ገለፃ ዘዴ መሆኑን ያሳያል፡፡

Davies (1981) እና በድሩ (1994) እንደገለፁት መምህራን ትምህርቱን ለማቅረብ የሚጠቀሙበት የማስተማሪያ ዘዴ በተማሪ ክፍል ተሳትፎ ላይ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ

ተግሪደሮት ሊያደርስ ይችላል፡፡ በመሆኑም መምህራን እንደ ትምህርቱ ይዘት የማስተማሪያ ዘዴ አቀያይረው የማይጠቀሙና ሁል ጊዜ በመምህሩ የሚመራ በገለፃ ዘዴ የሚያስተምሩ ተማሪዎችን በቡድን፣ በጥንድ፣ በግል ወዘተ ተማሪ አሳታፊ የማስተማር ዘዴ የማጥጠቀሙ ከሆነ የክፍል ውስጥ ተሳትፎን አሉታዊ በሆነ መንገድ ይወስናል ያሉትን ሀሳብ የሚጋራ ነው፡፡ በአጠቃላይ ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤት ከጽሁፍ መጠይቅ ፣ ከምልከታና ከቃለመጠ የጠገኙ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት ትምህርቱ በመምህሩ ብቻ የሚመራና የመረጃ ሁሉ ምንጭ መምህሩ ተደርጎ የሚታሰብበት፣ ተማሪዎች ከመምህሩ ብየሚቀርበውን ገለፃ ዝም ብለው ከማዳመጥ ያለፈ በትምህርቱ ላይ የጎላ ተሳትፎ ያልነበራቸው መሆኑን ያሳያሉ፡፡ይህ በመምህሩ ብቻ የሚመራ የቋንቋ ትምህርት የክፍል ውስጥ ተሳትፎን ከመገደቡም ባሻገር ተማሪዎች የቋንቋ እውቀትና ክሂል እንዳያዳብሩ ስለሚያደርግ መማር ማስተማሩን ይጎዳዋል፡፡ በመሆኑም የትምህርት አቀራረብ በአማርኛ ትምህርት የተማርዎችን ክፍል ተሳትፎ መምህሩ የሚገድብ ዘጠነኛ ደረጃ ተግዳሮት ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በስተመጨረሻም Rocca (2008) የተማሪዎች ፆታ የክፍል ተሳትፎን በአሉታዊ ወይም በአዎንታዊ መንገድ ሊወስን እንደሚችል ገልፀዋል፡፡ በዚህ ጥናት በምልከታ የተገኘው መረጃ ውጤት እንደሚያሳየው በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ የሚሞክሩት በአብዛኛው ወንዶች መሆናቸውን ለመታዘብ ተችሏል፡፡ በሌላ በኩል ከተማሪዎችና መምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘው መረጃም በተመሳሳይ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ያላቸው ወንድ ተማሪዎች መሆናቸውን አሳይቷል፡፡

ከጥናቱ ውጤት የምንገነዘበው በትምህርት ቤቱ ውስጥ የዘጠነኛ ክፍል ወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች የበለጠ ተሳትፎ ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህም petress (1978) በክፍል ውስጥ ባላቸው ተሳትፎ ወንድ ተማሪዎች ከሴት ተማሪዎች የበለጠ ተሳትፎ እንዳላቸው የገለፁትን ሀሳብ የሚያጠናክር ነው ስለዚህ ፆታ ዘጠነኛ ተግዳሮት እንደሆነ ለመረዳት ተችሏል ፡፡

### 4.2.2 የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚወስኑ ተግዳሮቶች በቋንቋ ትምህርት የሚያሳድሩትን አንድምታ መመርመር

የተማሪዎችን ከጥናቱ መሠረታዊ መላምት አንፃር በውጤት ትንተናው ሌላው ትኩረት የተደረገበት ጉዳይ በተማሪዎች ቋንቋ ክሂሎት ላይ ተግዳሮት መኖር አለመኖሩን መመርመር ስሆን ከተማዎች ክፍት የጽሁፍ መጠይቅ እና ከመምህራንና ተማሪዎች የተገኘው መረጃ ትንተና ውጤት ለመረዳት እንደተቻለው በተማሪዎች ቋንቋ ክሂሎት ላይ አሉታዊ ተግዳሮትን የሚያሳድሩ መሆናቸውን ያመላክታል፡፡ ይህም Warren (1997)፣ Tatar (2005) የጥናት ውጤቶች ጋሪ ተደጋጋፍነት አለው፡፡ ተግዳሮቶቹ ተማሪዎች እርስ በርስና ከመምህራቸው ጋሪ ተግባቦት እዳያደርጉ፣የቋንቋ ክሂልና ዕውቀት እንዳያዳብሩ የሚያደርጉ በመሆናቸው አሉታዊ ተግዳሮት እንዳለው የመረጃ ውጤት ትንተና አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት እንደሚያመለክተው በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች መኖራቸውን አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም በተማሪዎች ቋንቋ ክሂሎት ላይ አሉታዊ ተግዳሮት የሚያሳድሩ መሆናውን የውጤት ትንተናው ያመላክታል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## 5. ማጠቃለያና የመፍትሔ ሀሳብ

### 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በቱሪ ፤በታርጫ እና ማረሚያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መግለፅ ሲሆን ይህ ጥናት እንዲመልሳቸው የቀረቡት መሰረታዊ ጥያቄዎች ሀ. ለጥናቱ በተመረጠው ትምህርት ቤት በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ምንድን ናቸው?

ለ. የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች በቋንቋ ትምህርት የሚያሳድሩት አንድምታ ምንድን ነው? የሚሉት ነበሩ፡፡

እነዚህን ጥያቄዎች በትክክል ለመመለስ ይቻል ዘንድ የአጠናን ዘዴን የመወሰን፤ በጥናቱ የሚሳተፉ ተጠኝዎችና ተገቢ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የመምረጥ ስራ ተከናውኗል፡፡ በዚህ መሰረት ጥናቱ መጠናዊ የምርምር ስልትን መሰረት በማድረግ የተከናወነው ገላጭ የጥናት ስልት ተከትሎ ነው፡፡ በዚህ ጥናት ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ ተሳታፊዎችን (ተጠኝዎች) ለመምረጥ በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ ቱሪ ፤ታርጫ እና ማረሚያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ና መሰናዶ ትምህርት ቤት እና በትምህርት ቤቱ ከሚገኙት ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን በመምረጥ ተካሂዷል፡፡ በዚህ ትምህርት ቤት የሚገኙ አራት የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መምህራን በጠቅላይ ንሞና የተመረጡ ሲሆኑ በ2011 ዓ.ም ትምህርታቸውን እየተከታተሉ የሚገኙ 171 የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በዕኩል ዕድል ሰጭ የናሙና አመራረጥ ዘዴ የሆነውን ቀላል የዕጣ ንሞናን ተግባራዊ በማድረግ ተመርጧል ፡፡ ለጥናቱ መረጃ መሰቢሰቢያነት የተመረጡት የፅሁፍ መጠይቅ፣ ምልከታ እና የቃል መጠይቅ ናቸው፡፡ ከመጠይቁ የተገኘው መረጃ በኤስ ፒ ኤስኤስ(spss) ስታትስቲክስ ነጠላ ቲ-ቴስት(One sample t-test) ቀመር ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ከምልከታ የተገኘው መረጃ በድግግሞሽና በመቶኛ ተሰልቶ ውጤቱ በትንተናና በገለፃ ቀርቧል፡፡ ከቃለ መጠይቅ ከመምህራንና ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ በገለፃ መልክ ተተንትኗል፡፡

በፅሁፍ መጠይቅ የተሰበሰበውን መረጃ መሰረት በማድረግ በቅድሚያ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመለየት መረጃው በነጠላ ናሙና ቲ-ቴስት (one sample t-test) ተተንትኗል ዉጤቱም የሚያመላክተዉ ተግዳሮት መኖሩን ያሳያል በተጨማሪም የምልከታ እና የቃለ መጠይቅ ውጤት በተመሳሳይ የተማሪዎች ክፍል ተሳትፎን የሚገድቡ በርካታ ተግዳሮቶች መኖራቸውን አመላክቷል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የታየው መሪ ጥያቄ የተማሪ የክፍል ተሳትፎን የሚገድቡ ተግዳሮቶች በቋንቋ ትምህርት የሚያሳድሩት አንድምታ ለመመርመር በክፍት፤ ፅሁፍ መጠይቅና በቃለመጠይቅ በተሰበሰበው መረጃ አሉታዊ ተግዳሮት መኖሩን ለመረዳት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በቱሪ ፤ታርጫ እና ማረሚያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሳናዶ ትምህርት ቤት በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚወስኑ ተግዳሮቶችን ለመለየት በተደረገው ቅኝት የተገኘውን መረጃ በመተንተንና በውጤት ማብራሪያ ላይ በመመስረት ከሚከተሉት ማጠቃለያ ላይ ተደርሷል፡፡

- በቱሪ፤ ታርጫ እና ማረሚያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች መኖራቸውን ለመለየት ተችሏል፡፡
- የተማሪ ክፍል ተሳትፎ የሚወስኑ ተግዳሮቶች በቋንቋ ትምህርት ላይ አሉታዊ አንድምታ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመላክቷል፡፡

## 5.3 የመፍትሔ ሀሳብ

ከቀረበው የጥናት ውጤት በመነሳት አጥኝዋ የሚከተሉትን የመፍተሔ ሀሳቦች ጠቁማለች ፡፡ የተማሪዎች ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ልዩ ልዩ ተግዳሮቶች ቢኖሩም በዚህ ጥናት ውስጥ በክለሳ ድርሳን ከተገለፁትና ከጥናቱ ውጤት አንፃር በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡትን ተግዳሮቶችን በቀዳሚነት፣ በተከታይነትና በዝቅተኛ ደረጃ ብሎ ከተግዳሮቶች አንፃር በሦስት መክፈል ይቻላል ፡፡ በዚህም መሰረት፣

- በቀዳሚነት የሚመደቡ ተግዳሮቶች፡- የመምህሩ ባህር ፣ የመማር ማስተማር ሁኔታ እና ተነሳሽነት ናቸው ፡፡
- በመሆኑም የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማበረታታት፡-

- የትምህርቱን ይዘቶች አሳታፊ በሆነ ዘዴ በማቅረብ የክፍል ተሳትፏቸውን የሚገድቡ ተግዳሮቶችን መቀነስ ፡፡
- ትምህርት ቤቱ ከመንግስትና ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር በመቀናጀት ተጨማሪ መማሪያ ክፍሎችን በማሰራት በአንድ ክፍል ውስጥ የተማሪዎችን ቁጥር (የተማሪ ክፍል ጥምርታ) በመመጠን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚያሳድጉበት ሁኔታ ቢመቻች፡፡
- በክፍል ውስጥ ተማሪዎች ትምህርቱን ተረጋግተው በሰከነ መልክ እንዲማሩ የመማሪያ ክፍል አካላዊ ሁኔታ እና የክፍል ውስጥ አየር የተማሪዎች ሁኔታ ምቹ እንድሆን ማድረግ ፡፡
- መምህራን ከተማሪዎች ጋር ጤናማ ግንኙነት በመፍጠር፣ አዎንታዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠትና በማበረታታት ተነሳሽነታቸውን በማሳደግ ከጭንቀት ነጻ ሆነው የሚማሩበትን ምቹ የመማር ማስተማር አውድ መፍጠር ፡፡
- ተማሪዎቹ የሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች መሆናቸውን በመገንዘብ በሚፈጠሩት ስህተት እንዳይደናገጡና ከተሳትፎ ራሳቸውን እንዳይቀጥቡ በመርዳት በራስ መተማመናቸውን የሚያጎለብቱበትን ስልት በመቀየስ ማገዝ መፍትሔ ይሆናል፡፡

❖ በተከታይነት ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ደግሞ አመለካከትና ስብዕና ጭንቀት ሲሆኑ፣ የሚከተሉት መፍትሔ ተጠቁመዋል

- በአማርኛ ቋንቋ ለመናገር ያላቸውን አመለካከት ለመቅረፍ ተማሪዎች ቋንቋውን በመማራቸው ተጠቃሚ እንደሚሆኑ መምህራን ምክንያታዊ ማስረጃ በማቅረብና ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት እንዲያዳብሩ ማድረግ
- ከስብዕና አንፃር በቋንቋዉ የመናገር፤የመግባባት፤የመጠየቅ፤የመመለስ ፤አስተያየት የመስጠትና የመወያየት ዕድል ቢሰጣቸዉ ፡፡
- መምህራኖች ተማሪዎች ተረጋግተውና ከጭንቀት ነጻ ሆነው ትምህርታቸውን እንድከታተሉ በተከታታይነት እየመከሩ ብያበረታቱ፡፡

❖ በዝቅተኛ ደረጃ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ፆታ፣ቋንቋ ፤የትምህርት አቀራረብ ስሆን የሚከተሉት መፍትሔ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

- በፆታ ልዩነት ሳይፈጠር ሁሉም ተማሪዎች በቋንቋ ትምህርቱ እኩል ተሳትፎ የሚያደርጉበትን የማስተማር ስልት መምህራን ቢጠቀሙ ፡፡
- ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማር ሂደት ቢሳተፉ የቋንቋ ደረጃቸውን እንደሚያሳድጉ በማስገንዘብ ከቋንቋ ደረጃቸው ጋር በተያያዘ ያለባቸውን ጫና ብቀነስ ፡፡
  - መምህራኖች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንድያደርጉ በተከታታይነት ብያበረታቱ

በመጨረሻም የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎዋቸውን የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመቅለፍ የሚመለከታቸው አካላት ሁሉ በተለይ ለትምህርት ሥራ ቅድሚያ ቢሰጥ እያልኩ

- ለመምህራን ሥልጠና ቢሰጥ
- የተማሪ መጽሃፍትን ባለሙያ ቢያዘጋጅ ምክንያቱም እዛው ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ያሉ የሚሰሩበት ሁኔታዎች ስላሉ ቢፈተሽ የተሻለ ይሆናል፡፡

## ዋቢ መጽሃፎች


ስፍራሽ አሞኘ፡፡ (2002) ፡፡ በባህር ዳር ከተማ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የክፍል ውስጥ የትምህርት አቀራረብና የተማሪ ተሳትፎ.፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ 2ኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ቴስስ፡፡

በድሩ ከድር፡፡ (1994) ፡፡ የትምህርት ተከታታይ ምዘናና መሠረታዊ ፅንሰ ሀሳቦች ና ተክኒኮች ፡፡ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ድርጅት፤ አዲስ አበባ፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2004) ፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፤ አዲስ አበባ፤ 3ኛ እትም፡፡

ፋሲል መኳንት፡፡ (2002) ፡፡ የተማሪ ክፍል ውስጥ ተሳትፎና የአማርኛ ትምህርት ውጤት ተዛምዶ፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ 2ኛ ድግሪ ማሚያ የቀረበ ቴስስ፡፡

Bailey, K.M & Savage, L. (1994). New Ways in Teaching Speaking, Teachers of English to Speakers of Other Languages. Alexandria, VA: TESOL.

Barrett, L., & Connot, R. (1986). Knowing student personality can help school, classroom, Activity participation. *NASSP Bulletin, February*, (pp.39-45).

Beebe, L. M. (1983). Risk-taking and the language learner. In H. W. Seliger & M. H. Long (Eds.), Classroom *oriented research in second language acquisition* (pp. 39-66). Rowley, MA: Newbury House.

Brown, H.D. (1994). Principles of Language Learning and Teaching. (3th edition). New York: Longman, Inc

Brown, H.D. (2000). Principles of Language Learning and Teaching. (4th edition). New York: Longman, Inc

Berdine, R. (1986). Why some students fail to participate in class. Marketing News, 20 pp.23_24.(ASO)

Burchfield, C. M., & Sappington, J. (1999). Participation in classroom discussion. Teaching of Psychology,26,pp.290_291.(ES)

Cohen, M. (1991). Making class participation a reality. Political Science & Politics, 24, (4) pp.699_703.http://doi,org/10.2307/419408

Davies, I.K. (1981).Instructional Technique. USA. McGraw- hill

Daved, N. (2008). Students' Participaton in English Languag Classroom. University of Malaysia Sarawaka. pp1-24. ir.unimas. my/5692/1/

Dörnyei, Z. (2005). The Psychology of the Language Learner: Individual Differences in Second Language Acquisition.Lawrence Frcbaum Associates, Publshers Mahwah, New Jersey, London.

Edward, M. (2006). Improving you're Childs Classroom Participation. Center for Effective Parenting. Retrieve December20, 2014.

Fassinger, P. A. (1995a). Professors' and students' perceptions of why students participate in class.Teaching Sociology, 24, pp. 25_33. (ES)

Farrant; J, s .(1980). Principles and Practice on education London: Westerly Printing Serves Ltd.

Fritschner, L. M. (2000) Inside the undergraduate college classroom: Faculty and students Differ on the meaning of student participation. The Journal of Higher Education, 71, pp.342_362. (LR)

Gardner, R.C. (1985). Social Psychology and Second Language Learning: The Role of Attitudes and Motivation. London: Edward Arnold.

Gardner, R. C. & Lambert, W.E. (1972). Attitudes and Motivation in Second — Language Learning. Rowley, MA: Newbery House.

Green. D. (2008). Class Participation In Teacher Training College, what it is and what Factors Influence it? ELTEP, vol.11

Griffiths, R. (1991b). Personality and Second Language Learning: theory, research and Practice. www.ccsent.org/journal html ED367 167

Harmer .J. (2001).The practice of English language Teaching. Essex, UK: Pearson Education Limited.

Hill, M, T .(2007).Class Room participation.U.S, Military Academy, West point, NY.Karp, D. A., & Yoels, W. C. (1976). The college classroom: Some

observations on the meaning of student participation. Sociology and Social Research, 60, pp.421-439.

Krashen,S. (1982). Principles andpractce in second language Acquisition. Oxford: pergamon 5 Press, Inc

Lightbown, P. M & N. Spada (2006). How Languages are Learned. Oxford: Oxford University Press.

Lee. p (2005). Students personality type and altitude to ward Class room participation. California State University.

Le; Thi; mai. (2011). An investigation in to factors that hinder the participation of University students in English speaking Lesson. Http//life style . ilove India. com / Lounge /Characteristic of a good teacher -1807'htm/

Li ,H, &Liu ,Y .(2011).A brief Study of reticence in ESL Class Theory and practice in Language Studies.1(8)961-965' http://dx.doi.org /10.4304/.tpls.1.8.961-965

Liu, M,H. (2005). Reticence in oral English Language Class room :A case study in china .TESL Reporter,38(1) pp.1-16.

Liu, M,&. Jackson , J.(2008). An exploration of Chinese EFL Learners 'Un willingness to communicate and foreign language anxiety. Modern language,Journal.92(1)71-86 http://dx,doi;org//0,1111/J.1540-478/,00687,x

Mohan (1993). Educational psychology. India: wiley.Estern limited

Morrison, T. L. & Thomas, M. D. (1975). Self-esteem and classroom participation. The Journal of Educational Research, 68, 374_377. (ES)

Peters, R. A. (1978). Effects of anxiety, curiosity, and perceived instructor threat on student Verbal behavior in the college classroom. Journal of Educational Psychology, 70, 388_395. (ES)

Petress, K.(2000). An Operational Definition of class participation. Retrieved December 10,2009, From http//www,vmpi' maine, edu /petreess/Article AOl pdf

Pearson, J. C., & West, R. (1991). An initial investigation of the effects of gender on student questions in the classroom: Developing a descriptive

base. Communication Education, 40 23_32.(ES)
Rocca, K. A. (2009). Student Participation in the college classroom: An Extended Multidisciplinary literature review, National communication association. vol 59,no2, pp,185- 213
Schumann, J.H. (1975). Affective factors and problem of age in second language acquisition. Language Learning, 25/2, 209-235.
Scovel, T. (1978). The effect of affect on foreign language learning: a review of anxiety Research. Language Learning vol. 27, no.1, pp. 129-42.
Smith, D. H. (1992). Encouraging students' participation in large classes: A modest proposal. Teaching Sociology, 20, 337_339. (IT)
Sotto, E.(1994).When Teaching Become Learing.Gret Britan: Red Wood Books
Spielberger, C. (1983). Manual for tbe state-trait anxiety inventory Palo Alto, CA: Consulting Psychologists Press.
Stern, H. (1994). Fundamental Concepts of Language Learning. Oxford. Oxford University Press.
Tannen, D. (1992). How men and women use language differently in their lives and in the Classroom. The Education Digest, 57, 3_6. (ASO)
Tatar, S. (2005). Why keep silent? The class room participation experiences of non-native English communication, 5,284-293
Xu, R. (2006). Factors Affecting classroom oral participation of Teacher Learner' sinuous English Teaching .3(7): pp.58-62
Warren, R, G (1997). "Students in active learning" About campus 2, pp.16-201
Weaver, R. R. & Qi, J. (2005). Classroom organization and participation: College students'Perceptions. The Journal of Higher Education, 76, 570_601. (ES)
Williams, D. (1990). Is the post-secondary classroom a chilly one for women? A review of the literature. The Canadian Journal of Higher Education, 20, 29_42. (LR)

Williams, R. (1971). Relationship of class participation to personality, Ability, and Achievemen variables. The Journal of Social Psychology, 83, 193_198.

(ES)

# አባሪ (ሀ)

## ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነፅሑፍ  አማርኛ

## ትምህርት ክፍል ድህረ ምረቃ ፕሮግራም

## በተማሪ የሚሞላ መጠይቅ

ውድ ተማሪዎች ፡- የዚህ መጠይቅ ዓላማ በአማርኛ ትምህርት የተማሪዎችን የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ትንተና በሚለው ርዕስ ለሚጠናው ጥናት መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መጠይቅ አማካኝነት የተሰበሰበው መረጃ ለሌላ ዓላማ አይውልም ፡፡ ውድ ተማሪዎች በዚህ መጠይቅ ለቀረቡት ጥያቄዎች ግልፅና ትክክለኛ ምላሽ መስጠት የጥናቱን ውጤት ተቀባይነት እንዲኖረው ከፍተኛ ዕገዛ ያደርጋል፡፡ ስለሆነም ይህንን መጠይቅ በአግባቡ እንዲትሞሉልኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ፡፡ በመጠይቁ ላይ የሚሞሉት መረጃ በጥንቃቄ እድትሞሉልኝ እየጠየኩ ለሚታደርጉልኝ ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡- በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

የፅሑፍ መጠይቁን ከሌላ ጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት  አይፈቀድም፡፡

ክፍል አንድ፡- ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡት ዝርዝር ጥያቄዎች ለእያንዳንዳቸው አምስት አማራጭ መልሶች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ አማራጭ መልሶች በቁጥር የተሰየሙ ሲሆኑ ቁጥሮቹም የሚከተሉትን የመስማማት ደረጃ ይወክላሉ፡፡

5=በጣም እስማማለሁ 4=እስማማለሁ 3=ለመወሰን ያስቸግራል 2=አልስማማም 1 = በጣም አልስማማም

ለጥያቄዎቹ መልስ ይሆናል ብለው በሚስማሙት አማራጭ ትይዩ ይህን ≪×≫ ምልክት ያድርጉ ፡፡

| ተ/ቁ | ጥያቄዎች<br>አመለካከትን የተመለከቱ ጥያቄዎች | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን ይቸግረኛል | አልስማማም | በጣም አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በክፍል ውስጥ በአማረኛ መናገር ያስደስተኛል፡፡ | | | | | |
| 2 | መምህሩ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ጥያቄ ሲጠይቀኝ ለመመለስ ደስ ይለኛል፡፡ | | | | | |
| 3 | በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለማድረግ ሌሎች ተማሪዎች ከእኔ የተሻሉ ናቸው ብዬ አስባለሁ ፡፡ | | | | | |
| | **ጭንቀትን የተመለከቱ ጥያቄዎች** | | | | | |
| 4 | በክፍል ውስጥ በተማሪዎች ፊት በአማርኛ መናገር ያስጨንቀኛል ፡፡ | | | | | |
| 5 | በክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ለመሳተፍ እሳሰታለሁ ብዬ እፈራለሁ፡፡ | | | | | |
| 6 | በክፍል ውስጥ ከመምህሩ እና ከክፍል ጓደኞቼ ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ሳልጨነቅ ምላሽ እሰጣለው፡፡ | | | | | |
| 7 | በክፍል ውስጥ ወይይት የራሴን ሀሳብ ሳልፈራ እናገራለሁ፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | **ተነሳሽነትን የተመለከቱ ጥያቄዎች** | | | | | |
| 8 | ጥሩ ውጤት ለማግኘት ስል በክፍል ውስጥ ተግባራት ተሳትፎ አደርጋለሁ፡፡ | | | | | |
| 9 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ተሳትፎ ማድረግ ጠቀሜታ አለው፡፡ | | | | | |
| 10 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሳደርግ ወይም ስናገር የቋንቋ ስህተት ቢፈጠር ሌሎች ተማሪዎች ይስቁብኛል ብዬ እፈራለሁ ፡፡ | | | | | |
| | **ስብዕናን የተመለከቱ ጥያቄዎች** | | | | | |
| 11 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በንቃት እሳተፋለሁ፡፡ | | | | | |
| 12 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ማንኛውንም ያልተረዳሁት ጥያቄ እጠይቃለሁ ፡፡ | | | | | |
| 13 | በክፍል ውስጥ በፈቃደኝነት ተሳትፎ አደርጋለሁ፡፡ | | | | | |
| 14 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በወይይት፣ በጥያቄና መልስ መሳተፍ ያስደስተኛል፡፡ | | | | | |
| 15 | ከመምህርና ከተማሪዎች ጋር በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተሳትፎ አደርጋለሁ፡፡ | | | | | |
| 16 | በክፍል ውስጥ የሚሰጠኝን ተግባር ለማከናወን ፈቃደኛ ነኝ፡፡ | | | | | |
| 17 | የክፍል ጓደኞቼ ወይም መምህራን ስህተቴን ሲያርሙ ምንም ወይም ማስተካከያ ስሰጡ ለመቀበል ፈቃደኛ ነኝ ፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 18 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተሳትፎ ለማድረግ በራሴ እተማመናለሁ፡፡ | | | | | |
| 19 | በክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ከመናገር ዝምታን እመርጣለሁ፡፡ | | | | | |
| | **የተማሪዎችን ፆታ የተመለከቱ ጥያቄዎች** | | | | | |
| 20 | በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ ተግባራት ወንዶችናሴቶች በእኩል ተሳትፎ ያደርጋሉ፡፡ | | | | | |
| | **የተማሪ ቋንቋ የተመለከቱ ጥያቄዎች** | | | | | |
| 21 | በአማርኛ ቋንቋ እንደ አፊ-ፈት መናገር እችላለሁ፡፡ | | | | | |
| 22 | መምህሩ በአማርኛ ቋንቋ የሚናገረውን ነገር እረዳለሁ፡፡ | | | | | |
| | **የትምህርት አቀራረብ የተመለከቱ** | | | | | |
| 23 | መመህሩ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ በቡድን፣ በጥንድ እና በግል ያሳትፋሉ፡፡ | | | | | |
| 24 | የአማርኛ መምህር የትምህርቱ አቀራረብ አሳታፊ ነው፡፡ | | | | | |
| 25 | መምህሩ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ ጥያቄ አዘጋጅቶ ይጠይቃሉ፡፡ | | | | | |
| | **የመምህሩ ባህሪ የተመለከቱ ጥያቄዎች** | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 26 | ከአማርኛ መምህር ጋር መልካም ግንኙነት አለኝ፡፡ | | | | | |
| 27 | መምህሩ በክፍል ውስጥ ሲያስተምር ቁጡ ነው፡፡ | | | | | |
| | **የመማር ማስተማር ሁኔታ የተመለከቱ ጥያቄዎች** | | | | | |
| 28 | የመማርያ ክፍል ውስጥ አቀማመጥ ተሳትፎ ለማድረግ ምቹ ነው፡፡ | | | | | |
| 29 | የተማሪ ቁጥር ለክፍል ተሳትፎ ምቹ ነው፡፡ | | | | | |
| 30 | የመማሪያ ክፍል ውስጥ ሁኔታ ለመማር ማስተማር ምቹ ነው፡፡ | | | | | |

**ክፍል ሁለት**፡- ቀጥሎ ሁለት ክፍት ጥያቄዎች ቀርበዋል እነዚህን ጥያቄዎች በሚገባ አንብበው ተገቢ መልስ ስጡ

31 በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት ናቸው ብላችሁ የሚታስቡትን ግለፁ?

--------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------------------------------------------------------------------------------------------------
--------------------

32. በተማሪ ክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት ይሆናሉ ያላችሁት ለቋንቋ ትምህርት ያለው ጫና ምንድን ነው

## አባሪ (ለ)

### ከተማሪዎች አንፃር የክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመፈተሽ በክፍል ውስጥ ምልከታ በአጥኝዋ የሚሞላ

| ተ.ቁ | ተማሪዎችን የተመለከቱ | አማራጮች | |
|---|---|---|---|
| | | አዎን | አይደለም |
| 1 | ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ፍላጎትና ተነሳሽነት አላቸው? | | |
| 2 | በክፍል ውስጥ የቡድን ውይይት ሁሉም ተማሪዎች ይሳተፋሉ? | | |
| 3 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ያልተረዱትን ጥያቄ ይጠይቃሉ? | | |
| 4 | ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በንቃት ይሳተፋሉ? | | |
| 5 | በክፍል ውስጥ ለሚጠየቁት ጥያቄ ሳይፈሩ ምላሽ ይሰጣሉ? | | |
| 6 | በክፍል ውስጥ በፈቃደኝነት ተሳትፎ ያደርጋሉ? | | |
| 7 | በክፍል ውስጥ በአማርኛ ቋንቋ ሳይጨናነቁ ይናገራሉ? | | |
| 8 | በክፍል ውስጥ በቡድን ወይም በጥንድ በሚሰሩት ተግባር ላይ ከጓደኞቻቸው ጋር ሳይፈሩ ይወያያሉ? | | |
| 9 | ከመምህራቸው ወይም ከጓደኞቻቸው ጋር ነፃ ሆነው በክፍል ውስጥ ተሳትፎ | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | ያደርጋሉ? | | |
| 10 | በአማርኛ ለመናገር ይፈልጋሉ? | | |
| 11 | በክፍል ውስጥ በቡድን፣ በጥንድና በግል ተሳትፎ ያደርጋሉ? | | |
| 12 | ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት ኃላፊነት ይወጣሉ? | | |
| 13 | ተማሪዎች በመማር ማስተማር ሂደት አስተያየት ይሰጣሉ? | | |
| 14 | በክፍል ውስጥ ወንዶችና ሴቶች በእኩል ደረጃ ይሳተፋሉ? | | |

## አባሪ (ሐ)

### ከመምህራን አንፃር የተማሪ ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶችን ለመለየት

በክፍል ምልከታ  የሚሞላ

| ተ.ቁ | መምህራንን የተመለከቱ | | |
|---|---|---|---|
| | | አዎን | አይደለም |
| 1 | መምህሩ ተማሪዎች ምን መስራት እንዳለባቸው ግልፅና ቀላል መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ይሰጣል? | | |
| 2 | መምህሩ ለተማሪዎች ጥያቄ ተገቢ ምላሽ ይሰጣል? | | |
| 3 | መምህሩ ከተማሪዎች ጋር መልካም ግንኙነት አለው? | | |
| 4 | ተማሪዎችን በስም እየጠራ መምህሩ ያሳትፋል? | | |
| 5 | መምህሩ ሁሉን ተማሪ በእኩል ያሳትፋል? | | |
| 6 | የመምህሩ ባህሪ ለመማር ማስተማር ምቹ ነው? | | |
| 7 | መምህሩ የተማሪዎችን ተሳትፎ ያበረታታል? | | |
| 8 | መምህሩ እንደ ትምህርቱ አቀራረብ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴ እያለዋወጠ ይጠቀማል? | | |
| 9 | የክፍል ውስጥ የተማሪ አቀማመጥ ለተሳትፎ ምቹ ነው? | | |
| 10 | የተማሪዎች ቁጥር ለተሳትፎ ምቹ ነው? | | |
| 11 | የመማሪያ ክፍል  ለመማር ማስተማር ምቹ ነው? | | |

# አባሪ (መ)

## በተማሪዎች የሚመለስ የቃለ መጠይቅ ጥያቄ

የተጠያቂ ስም -----------

ቀን,-------------------------

የቃለ መጠይቁ አላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚወስኑ ተግዳሮቶች ትንተና ? በሚለው ርዕስ ለሚጠናው ጥናት ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ በመሆኑም የእርሶ ምላሽ ለጥናቱ ውጤት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ስላለው የሚሰጡኝ ምላሽ ከጥናቱ አላማ ውጭ የማይውል መሆኑን በአክብሮት እገልፃለሁ፡፡

1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የክፍል ተሳትፎ እንዳታደርጉ ችግር የሚፈጥሩባቸው መሰናክሎች ምንድናቸው?

--------------------------------------------------------------------------------------------------

--------------------------------------------------------------------------------------------------

2. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚወስኑ ተግዳሮት

ለቋንቋ ትምህርት ዕድገት ተግዳሮት አለው ብለው ያስባሉ ?

አለ ካሉ ምን አይነት ተግዳሮት አለው?------------------------------------------------------

3. በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተሳትፎ ለማድረግ ትፈራላችሁ? የሚያስፈሯችሁ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው ?

-------------------------------------------------------------------------------------

---------------------------------------------------------------------------------------

4. በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተማሪ አሳታፊ የማስተማሪያ ዘዴ መምህሩ ይጠቀማሉ? የሚጠቀሙ ከሆነ በምን አይነት መንገድ እንድትሳተፉ ያደርጋሉ?------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------

5. በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ከወንድ እና ከሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የበለጠ ተሳትፎ የሚያደርጉት የትኞቹ ናቸው? ለምን?

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

6. አማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላችሁ ፍላጎት ምን ይመስላል? ------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

7. መምህራችሁ በክፍል ውስጥ ትምህርት በእኩል ያሳትፋሉ? --------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------------------

8. መምህራችሁ በተለያዩ ሥራ ተሳትፎ ስታደርጉ ያበረታታሉ? ለተሳትፎ አዎንታዊ

ምላሽ ይሰጣሉ? --------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------

## አባሪ (ሠ)

ለመምህራን የሚቀርብ ቃለ መጠይቅ

የተጠያቂ ስም-----------------------------------------

አድራሻ-------------------------------------------

የስራ ክፍል---------------------------------------

የቃለ መጠይቁ አላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚገድቡ ተግዳሮቶች ትንተና ? በሚለው ርዕስ ለሚጠናው ጥናት ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡

በመሆኑም የእርሶ ምላሽ ለጥናቱ ውጤት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስላለው የሚሰጡልኝ ምላሽ ከጥናቱ አላማ ውጭ የማይውል መሆኑን በማክበር እገልፃለሁ፡፡

1. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ተግዳሮት የሚሆኑ መሰናክሎች ምንድን ናቸው?-------------------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

2. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎችን ክፍል ተሳትፎ የሚወስኑ ተግዳሮት በቋንቋ ትምህርት ተግዳሮት ይኖራል ብለው ያስባሉ ?

   አለ ካሉ ምን አይነት ተግዳሮት አለው?

3. በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ተማሪዎች ተሳትፎ ለማድረግ ይፈራሉ ብለው ያስባሉ? ምክንያቱ ምንድነው?------------------------------------------------------------------------------------------

-----------------------------------------------------------------------------------------------

4. አሳታፊ የማስተማር ዘዴ በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ይጠቀማሉ? የሚጠቀሙ ከሆነ በምን አይነት ዘዴ እንዲሳተፉ ያደርጋሉ?----------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

5. በአማርኛ ክፍለ ጊዜ ከወንድ እና ከሴት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የበለጠ ተሳትፎ የሚያደርጉት የትኞቹ ናቸው? ለምን?---------------------------------------------------------

-------------------------------------------------------------------------------------------

6. ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል

----------------------------------------------------------------------------------------------------

------------------------------------------------------------------------------------------------------

7. በክፍል ውስጥ ተግባራት ተማሪዎችን በእኩል ያሳትፋሉ?

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

----------------------------------------------------------------------------------------------------------------

8. ተማሪዎች በተለያዩ ተግባራት ተሳትፎ ሲያደርጉ ያበረታታሉ? ለተማሪዎች ተሳትፎ አዎንታዊ  ምላሽ ይሰጣሉ?-------------------------------